# የስሕተት ትምህርቶችና ልምምዶች ባህርያት

የሐሰት ትምህርቶችና ልምምዶች በአጠቃላይ እሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ያሉት በስም የታወቁ የሐሰት ትምህርቶች በአንድ በኩል ሲገኙ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙት የስሕተት ትምህርቶችናልምምዶች ደግሞ በአንድ በኩል ሊፈረጁ ይችላሉ። ይህ መጽሐፍ እንደመጀመሪያው መጽሐፍ ሁሉ ግቡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉት የተሳሳቱ ልምምዶች ላይ ማተኮር ነው። ሆኖም በዚህ አጋጣሚ የሌሎቹን ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ያሉትን መጽሐፍ ቅዱስን የሚጋሩ የስሕተት እምነቶች ባህርያት በመጠኑ ማወቁ አስፈላጊ ይሆናል። ምክንያቱም አንዳንዶቹ ነጥቦች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙ የተሳሳቱ ልምምዶች ጋርም ይቀራረባሉ። በዚህኛው አሳብ ስር የተወሰዱት ትልልቅና ዋና ነጥቦች ዶክተር አንተኒ ሂኪማ የተባለ ሰው ከጻፈው መጽሐፍ ነው።[25]

የስሕተት እምነቶች ወይም ሃይማኖቶች የምንላቸው እንደ ይሆዋ ምስክሮች፥ ሞርመኖች፥ እና የመሳሰሉት ናቸው። የስሕተት እምነቶች የመጀመሪያው መለያ ባህርያቸው ከታሪካዊ ክርስትናና ከክርስትና የእምነት መግለጫዎች በድንገትና በፍጥነት ግንጥል ብሎ መውጣት ነው። እነዚህ ሃይማኖቶች ታሪካዊውን ክርስትናና እስከ እነርሱ ሃይማኖት ጅማሬ ድረስ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን እንደ ከሃዲ፥ ትምህርትዋን በሙሉም እንደ ክህደት በመቁጠር ለእነርሱ አዲስ ብርሃን እንደበራላቸውና እውነትን የመጠበቅ ኃላፊነት እንደተሰጣቸውም አስመስለው ይነሣሉ።

ሁለተኛ፥ ተነጥለው በወጡ ጥቂት ንዑሳን ትምህርቶች ብቻ ላይ ማተኮርና ዐበይት አስተምህሮዎችን ወደ ጎን ማድረግ። ለምሳሌ፥ የይሆዋ ምስክሮች ነን የሚሉ በክርስቶስ ትምህርት ከመኖር ይልቅ ከቤት እቤት ማንኳኳትና በመንገድ ማዕዘን መቆምን የሚሰጡት ግምት ይበልጣል። ሞርመኖችም ሰማያዊ ፍስሐና ጋብቻን እንዲሁም ለሙታን መጠመቅን እንደ ዋና ማየታቸው ጥቂቶቹ ናቸው።

ሦስተኛው ፍጹምነት ወይም ፍጹማዊነት ነው። ይህ በመጠኑ ከመጀመሪያው ነጥብ ጋር የሚቀራረብ ነው። በስሕተት እምነቶች ዘንድ ሌሎች እምነቶች ሁሉ የተሳሳቱና የጎደሉ፤ እነርሱና እነርሱ ብቻ ደግሞ ፍጹማንና ብቁአን እንደሆኑ ማወጅ የታወቀ ባህርይ ነው። መሥራቾቻቸው የመጨረሻውን መገለጥ ከእግዚአብሔር

---

25 Hoekema, pp. 373-88.





እንደተቀበሉና ከዓለም መጨረሻ በፊት የሚገኙት ብቸኞች የእምነት ሰዎች እነርሱ ብቻ እንደሆኑ አጥብቀው ያስባሉ። ከዚህም ጋር እነርሱ ብቻ በዚህ ዘመን የቀሩ የእግዚአብሔር ቅሬታዎች ወይም ሕዝቦች እንደሆኑና በዚህ የመጨረሻ ዘመን ግንባር ቀደምና ኮከብ ተዋናዮች እነርሱና የእነርሱ ሃይማኖት ሰዎች ብቻ እንደሚሆኑ ያስተምራሉ። የይሆዋ ምስክሮች ነን ባዮች በራእ. 7፥1-8 እና 14፥1-5 የተጠቀሱት 144ቱ ሺህ እነርሱ ወይም ከእነርሱ ሃይማኖት የተመረጡ ሰዎች መሆናቸውንም እንዳልተሳሳቱ ሆነው በትልቅ እርግጠኝነት ያስተምራሉ።

አራተኛ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላና ከመጽሐፍ ቅዱስ ካልበለጠ የማያንስ የተለየ የሥልጣን ምንጭ አላቸው። ይህ ብዙውን ጊዜ የሃይማኖቱ መሥራቾች የጻፉት መጽሐፍ ነው። ለምሳሌ፥ የክርስቲያን ሳይንስ እምነት ተከታዮችና ሞርመኖች እንዲህ ያሉ መጻሕፍት አሉአቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ የተለየ መጽሐፍ የላቸውም፤ ግን በራሳቸው ሰዎች የነርሱን ትምህርት እንዲደግፍ ተደርጎ የተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱስ አላቸው። ለምሳሌ፥ የይሆዋ ምስክሮች ነን የሚሉ *The New World Translation* የሚሉት ትርጉም አላቸው። እነማን እንደተረጎሙት እነርሱም ራሳቸው ደፍረው የማይናገሩት ብልሹ ትርጉም ነው። የኢየሱስን ፍጡር መሆን ለማስረዳት ሲጥሩ መጽሐፍ ቅዱስን እንዳይሆን እያደረጉ መበለታቸውና አጨማልቀው ሊተረጉሙ መሞከራቸው የዚህ የሌላ ሥልጣን ምንጭ ምሳሌ ነው። ከፕሮቴስታንት ሃይማኖታዊ ተሐድሶ ዋና ነጥቦች አንዱ፥ 'መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ' የሚል ነበር። በዘመኑ ከቃሉ ውጪ የሆኑ ሥልጣን እንዳላቸው የሚነገርላቸው ትምህርቶች ይሰራጩ ነበርና ይህን በመቃወም የተሰጠ አቋም ነበር። ይህም ለክርስትና እምነትና አኗኗር ዋናውና ብቸኛው መመሪያና የሥልጣን ምንጭ ቃሉ ብቻ ነው የሚል ነው።

አምስተኛው ደኅንነትን በተመለከተ የሚሰጡት የተዛባና የተጣመመ ትምህርት ነው። ደኅንነትን አስመልክቶ መሠረታዊው የክርስትና አስተምህሮ ደኅንነት ወይም ጽድቅ በክርስቶስ በኩል በሚገኝ ጸጋ ወይም እምነት ብቻ መሆኑን ነው። እነዚህ ሃይማኖቶች ግን ጽድቅን እንደ ሰማያዊ ሽልማት አድርጎ በማቅረብ ይህም በጸጋ ሳይሆን በሥራ ወይም በጸጋ ሲደመር በሥራ መሆኑን ያስተምራሉ። ሥራ ብለው የሚያቀርቡትም የራሳቸውን ሃይማኖታዊ ማኅበር ሥራ ነው። ከፕሮቴስታንት ሃይማኖታዊ ተሐድሶ ነጥቦች ሌላዎቹ፥ 'ጸጋ ብቻ' እና 'እምነት ብቻ' የሚሉ ነበሩ። በዘመኑ ሰው የሚድነው ወይም ጽድቅን የሚጎናጸፈው በሥራም እንደሆነ ይነገር ነበርና ይህን በመቃወም የተሰጠ ትምህርታዊ አቋም ነው።

ስድስተኛው ክርስቶስን በተመለከተ የሚሰጡት የተዛባና የተጣመመ ትምህርት ነው። የክርስትና እምነት በክርስቶስ

ትምህርት ብቻ ሳይሆን በራሱ በክርስቶስ ማንነት ላይ የተመሠረተ ነውና ሃይማኖቶች ስለ ክርስቶስ የሚሰጡት ትምህርት እንደ ዋና ሊታይ የተገባው ነው። በሐሰተኛ ሃይማኖቶች ዘንድ የክርስቶስን አምላክነት መካድ፥ ፍጡር ብቻ ማድረግ፥ ሰው ብቻ ማድረግ ይገኙበታል። የይሆዋ ምስክር ነን የሚሉ ክርስቶስን የተፈጠረ አምላክ ብቻ ሳይሆን መልአኩ ሚካኤልን ያደርጉታል።

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ከቤተ ክርስቲያን ክልል ውጪ የሚገኙ የሐሰተኛ ሃይማኖቶች ባህርያት ናቸው። እነዚህ ባህርያት ብዙውን ጊዜ ያገጠጡና የሚታዩ በመሆናቸው ብዙዎቻችን አንስታቸውም፤ እንጠነቀቃለንም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙት የስሕተት ልምምዶችና የስሕተት ዘሮች እጅግ እውነት መስለው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየኖሩና የቤተ ክርስቲያንን ጡት እየጠቡ ያደጉ በመሆናቸው አሳችነታቸው የሰፋ እንጂ ያነሰ አይደለም። የዚህ መጽሐፍ ግብ እንደመጀመሪያው መጽሐፍ ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምንሰማቸውና በምናያቸው የተሳሳቱና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ልምምዶችና ትምህርቶች ላይ ማተኮር ነው።

ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች ከቤተ ክርስቲያን ውጪ የሚገኙ የስሕተት ሃይማኖቶች ባህርያት ቢሆኑም በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ከነዚህ ትምህርቶች ጋር በሩቅ የሚገናኙ ልምምዶች ይገኛሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ የስሕተት ትምህርቶችና ልምምዶች የራሳቸው የሆኑ የተለያዩ ባህርያት አላቸው። ከእነዚህ ትምህርቶችና ልምምዶች መካከል እንደ ዋና ዋና የታዩኝ የሚከተሉት ናቸው።

*1፥ _ስሜትን በሚማርኩ ነገሮችና ትምህርቶች ዙሪያ መሽከርከር_።* ሀብት ወይም ብልጽግና፥ ጤንነት፥ ሥጋዊና ዓለማዊ ምቾትና ድሎት፥ በቀላሉ የሚለማመዱአቸው አንድና ሁለት የጸጋ ስጦታዎች እንዲሁም እነዚህን በመሳሰሉ ነገሮች ዙሪያ ብቻ ነው ትምህርቶቹ የሚሰጡት። በወንጌል ስርጭት፥ የወንጌል መልእክተኞችን በመላክና በመርዳት፥ ደቀመዛሙርትን በማድረግ፥ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን በመደገፍ፥ ችግረኞችን በመርዳት ሳይሆን በአመዛኙ ወይም በሙሉ ከግለ ሰቦች ጋር በተቆራኙና ስሜታዊ በሆኑ ልምምዶች ላይ ያተኩራሉ። በቃሉ ውስጥ የማይገኙና ለሥጋዊ አእምሮ የሚጥሙ አዳዲስና የሚስቡ ቃላትና ሐረጎችን በመፍጠርና በመጠቀምም መመዘን የማይችሉ የዋሆችን በቀላሉ የሚወስዱ ትምህርቶች ናቸው።

ብልጽግና ጥሩ ነገር ሊሆን ይችላል። ገንዘብ ያለጥርጥር መልካም አገልጋይ ሊሆን የሚችል መሣሪያ ነው። ነገር ግን ያልተሰጠንን ተስፋ ከቃሉ ውስጥ በጥሶ እያወጡ የሀብትና የብልጽግና ተስፋ እጾላ ሰዎችን ከትጋት ወደ ስንፍና የሚነዳ ብቻ ሳይሆን ለገንዘብና ለምድራዊ ሀብት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ አመለካከትን በልቡናቸው የሚያሰርጽ አደገኛ ትምህርት ነው።





እግዚአብሔር የሚፈውስ አምላክ ቢሆንም፥ የፈውስ ጸጋ ዛሬም ያለ ቢሆንም የውሸት ፈውሶች ብዙዎችን ቅር እያሰኙ ናቸው። የአገልጋዮቹን እውነተኛነት እጥያቄ ውስጥ ይከትታሉ፤ በዚህ ብቻ አያበቃም፥ ያልተፈወሱ ሰዎች በእምነት ማጣታቸው ራሳቸውን ይኮንናሉ፥ በእግዚአብሔርም ቅር ይሰኛሉ። በካሪዝማዊ ስብሰባና ኮንፍራንሶች እጅግ ብዙ ፈውሶች በሽተኞቹ ተጸልዮላቸው ሳይሆን እዚያ ጉባኤ ላይ ስለተገኙ ብቻ የሚታደሉት ቸርነትም ይመስላል። አንድ የፈውስ ስጦታ አለኝ ባይ በአንድ ጉባኤ ሲያገለግል በዚያ ለነበሩ ጥርሳቸው ላለቀባቸው ሰዎች ጌታ የወርቅ ጥርስ እንደሞላላቸው ተናገረ። የተፈጥሮ ሳይሆን የወርቅ ጥርስ። ይህ ጥርስ እንደተሞላላቸው በሐሰት የመሰከሩም ነበሩ። ምዕመናንም ሆኑ መሪዎች እንዲህ የመሰለውን እንግዳ ፈውስ ያለምንም ጥያቄ የተቀበሉት ይመስሉ ነበር። ኤድስን በተመለከተም በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ጥቂት ተጽፎአል።

*2፥ _ግብታዊነት_።* ይህ ማለት ድንገተኛና ያልታሰቡ ነገሮችን ማድረግን መለማመድ ነው። ነዋሪና ቋሚ መርሆዎችን በመናቅና በማጥላላት እነዚህ ጊዜ ያለፈባቸው ሰው ሠራሽ ሕግጋትና ደንቦች በማድረግ አጣጥሎ ያልተለመዱና በራሳቸው የተፈጠሩ ሥርዓቶችን መፍጠር ሌላው ባህርያቸው ነው። ይህን ብዙ ጊዜ የሚያደርጉት የአምልኮ መሪዎችና ሰባኪዎች ናቸው። ለዚህ አድራጎት ዋናው ማመካኛቸው መንፈስ ቅዱስ እየመራቸው እንደሆነ መናገር ነው። በተለይም የጉባኤን ሞቅታና የሰዎችን ስሜት ብቻ በመለካት የታሰቡና የተሰናዱ ነገሮችን ባልታሰቡና ባልታቀዱ ነገሮች መቀየር፤ ጉባኤውን አሜንና እልል የሚያሰኙ የተመረጡና የተለመዱ ዐረፍተ ነገሮችን በመደጋገም አስፈላጊ ሥርዓትን በአላስፈላጊ የመፈክር ጬኸት መለወጥና አንድን አዝማች እስኪያፈዝ፥ እስኪያደነግዝ ድረስ ለአሥርና ለሃያ ደቂቃ ያህል ሳይለውጡ መደጋገም በነዚህ ዘንድ የተለመደ ነው። ዕቅድና ዝግጅትን የሰው ሥራ፥ ግብታዊነትን የመንፈስ ቅዱስ አሠራር አድርገው ተቀብለውታል። ሰባኪዎችም የተሰናዱበትን ስብከት ትተው ከጉባኤው ሙቀት ጋር የሚመጣጠን ሌላ ያላዘጋጁትን ነገር ሊሰብኩ ይታገላሉ። ያልተዘጋጁበትን ሲናገሩ ስሕተቱም የዚያን ያህል ነው። በእርግጥ ስብከትን መለወጥ ሁሌም ግብታዊነት ላይሆን ይችላል። ይህ አንዳንዴ በጤናማ ሁናቴ ሊደረግ የሚችል ነገር ነው። ሆኖም እግዚአብሔር የሰዎችን ሁኔታና ስሜት ላለመጉዳት ሲል እውነትን በጊዜው ከመናገር ይልቅ ሌላ ጊዜ፥ ሌላ ቦታና አመቺ ሁኔታ የሚፈልግ አምላክ አይደለም። አንዳንዶችም ያለመዘጋጀታቸውን በዚህ ሰበብ ሊሸፍኑ ይሞክራሉ። የተዘጋጁት ወይም የተሰጣቸው ርእስ ሌላ ሆኖ መንፈስ ቅዱስ ግን እንዳስቀየራቸው ይናገራሉ። ብዙውን ጊዜ እንዲህ የሚሉ ሰዎች ወይ ቀድሞም አልተዘጋጁም፤ ያለዚያም በዚያን ጊዜ የሚሆነውን ስሜታቸውን ሰምተው እየተከተሉ ናቸው ማለት ነው። አስቀድሞ ተዘጋጅተው ከሆነ መንፈስ ቅዱስ ረድቶአቸው አይደለም የተዘጋጁት ማለት ነው፤

ምክንያቱም እንደሚቀየር መንፈስ ቅዱስ ያውቅ ነበርና። ይህም ግብታዊነት ነው።

በአምልኮ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላ የአመራር አቋም ደረጃም የእነዚህ ማኅበራት መሪዎች ሁሉ ሊከተሉት የተገባቸው ውሳኔዎችንም በግብታዊነት ይወስናሉ። በ1980ዎቹ አጋማሽ አቤንዔዘር የሚል ስም ለራሳቸው ሰጥተው ደብረ ዘይት አጠገብ ዋሻ ገብተው ሰንብተው የተመለሱ ወጣቶች ነበሩ። በኋላ የተሰማው ታሪካቸው ክፉ ነበር። በ1980ዎቹ መጨረሻ ደግሞ ሌላ ቡድን 'ዲኖሚኔሽን እርግማን ነው፤ እግዚአብሔር ዲኖሚኔሽንን በእኛ አድርጎ ያጠፋል' የሚል አርማ ይዘው ኢሉባቦር ጫካ የገቡ ነበሩ። የእነዚህን መጨረሻ አላወቅኩም። ይህ ቀደም ሲል ካየነው ከጂም ጆንስ ታሪክ ጋር በመጠን ይለያይ እንጂ በዓይነት ተቀራራቢ ነው።

3፥ <u>*ከወቀሳ በላይ የሆነ ሥልጣንና ትንቢታዊ ማስፈራራት*</u>። በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ውስጥ ሥልጣን ጤናማ ስፍራ አለው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ሆኑ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ተገቢ ስፍራና ክብር አላቸው። በስሕተት ልምምዶችና ትምህርቶች ቡድኖች መሪዎች ዘንድ ግን ሌሎች ሥልጣናትን መና ቅ ብቻ ሳይሆን ገደብ የሌለውን የራሳቸውን ሥልጣን ያለምንም ጥያቄ እንዲቀበሉ ተከታዮችን በግልጽና በስውር የማስገደድ ባህርይም ይታያል። ትንቢትንና ራእዮችን መሳሪያ በማድረግም ራስን ከፍ ማድረግ ብቻ ሳይሆን የእነርሱን ሥልጣን ደፍረው የሚጠይቁትን ሰዎች ለማስፈራራትም ይገለገሉበታል። ስለ ቅባት እንዳይሆን የሆነ ትምህርት በማስተማር ቅባታቸውን ከወቀሳ ነፃ መሆኛቸው አድርገውም እንደ ጋሻ ያነሡታል። ከዚህ ጋር የእነርሱን ትምህርት የሚወቅሱትን ብቻ ሳይሆን የማይቀበሉ ሁሉ አጋንንት እንዳለባቸው አድርጎ መናገር ነው። ንቅናቄው አጋንንትን በተመለከተ ያለው ትምህርት በብዙው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማይገኝ ነው። አጋንንት ከሰዎች ውስጥ ከመውጣታቸው በፊት የሚናገሩትን ነገር ሁሉ እንደ ትምህርት አድርገው የሚወስዱትም ይመስላል። የመናፍስቱ ብዛት፥ ዓይነት፥ ስማቸው፥ አጋንንቱ በክርስቲያኖች ላይ ያላቸው የተጋነነ ዘሎ ገብነትና ሥልጣን በአብዛኛው የተፈጠረ ነው። በአንድ ወቅት ከክርስቲያኖች ውስጥ አጋንንት እናወጣለን የሚሉ ሰዎችም ራሳቸውን 'አርነት' ብለው ተነሥተው ነበር። ቃሉን አጢነው የማያውቁ የዋሆች ይፈራሉ አጋንንትም ያለባቸው ይመስላቸዋል። ስለዚህ እንዲጸልዩላቸው ይፈቅዳሉ። አጋንንቱ ከሚወጡበት መንገዶች አንዱ፥ ለምሳሌ፥ በማስገሳት ሲሆን እርሱ በወጣበት መንፈስ ቅዱስ የሚገባው ደግሞ አየር ወደ ውስጥ በመሳብ ነው። ስለዚህ ሰዎች እንዲያገሱና ሳንባቸው እስኪያብጥ አየር እንዲምጉ ይደረጉ ነበር።





4፥ <u>*ዐውደ ወጥነት*</u>። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ የስሕተት ልምምዶች ዘንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ሥልጣን ያለው መጽሐፍ የለም። ግን ይህንን መጽሐፍ ቅዱስ እንዳይሆን አድርገው ያላለውን እንዲል ያደርጉታል። አብዛኛውን ጊዜ ይህ የሚሆነው በዐውደ ወጥ የጥቅሶች አመራረጥ ነው። ይህ ስሕተት ሰባኪዎቹ የሚሰብኩበት ወይም የሚጠቅሱት ጥቅስ ዐውደ ምንባብ ወይም ጠቅላላ ክፍሉ የሚለውን አሳብ በቸልታ ወደ ጎን ትቶ አንድዋን ቃል ወይም ሐረግ ብቻ ምዝዝ አድርጎ በማውጣት ሊያስተምሩ የፈለጉትን ነገር እንዲል ማድረግ ወይም ማስደረግ ነው። የጥቅስ የቅርብ ዐውደ ምንባብ ከፊቱና ከኋላው ያሉት ጥቅሶች ወይም አንቀጹ በሙሉ ሊሆን ይችላል፤ ሰፊው ዐውድ ግን ጠቅላላው ምዕራፍ ወይም ጠቅላላው መጽሐፍም ሊሆን ይችላል። በተወሰነ ትምህርት ላይ የጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ አሳብም ሊጤን የተገባው ዋና ነገር ነው። እንዲህ ያሉ አስተማሪዎች ብዙውን ጊዜ ወይም ሁሌም የሚሰብኩት አንድ ክፍልን ወይም መጽሐፍን ወስዶ ሳይሆን በርዕሳዊ ስብከት ስር በቃል የሚመሳሰሉ ጥቅሶችን ከዚህም ከዚያም በመቀነጣጠብ እንደ ጾቃ ቀጣጥሎ በዚያ ላይ በማተኮር ነው። ይህ ሲደረግ የጥቅሶች ዐውድ በቀላሉ ይሳታል፤ ወይም ይዘለላል። አንድ ቃል ወይም ሐረግ ወይም ዐረፍተ ነገር ምንም የእግዚአብሔር ቃል ቢሆን የተጻፈበት የምንባቡ ክፍለ አካል እንዳልሆነ ሁሉ ለብቻው ወጥቶ እንዲቆም ሲደረግ ለስሕተት አሠራር እንዲጋለጥ ማድረግ ነው። ለዚህ ታናሽ መፍትሔ ይሆን ዘንድ የመጽሐፍ ቅዱስን መጻሕፍት እንዴት ማየት እንደሚኖርብን የተሰናዳ ራሱን የቻለ ምዕራፍ ከዚህ ምዕራፍ ቀጥሎ ይገኛል።

5፥ <u>*ልምምዳዊነትና ኩረጃ*</u>። ይህ 'የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል?' ሳይሆን፥ 'ውጤቱ ምን ሆነ? ምን ተፈጸመ?' በሚሉ ጥያቄዎች ላይ ማተኮር ነው። ምንም ሆኖ በውጤቱ የሚፈለገው ነገር ከተፈጸመ ግብ ተቆጠረ ማለት ነው። በዚህ ነገር ውስጥ የተዘነጋ ነገር አለ፤ ያም፥ የተገኘው ነገር ወይም ውጤት የተገኘበትን መንገድ ሁሌም ትክክለኛ ሊያደርገው ያለመቻሉ ነው። በሽተኞችን ለመፈወስ፥ ሰዎች በልሳናት እንዲናገሩ ለማድረግ፥ ለማበልጸግ፥ ወዘተ አንዱ ከሌላው እየኮረጀ የሚለማመዱአቸው ልምምዶች ከቃሉ ትምህርት የራቁና የተጋጩ ብቻ ሳይሆኑ፥ 'ከሠራ ይሁን እንቀበለው፥ ጥቅም ከሰጠ በተግባር ላይ እናውለው' ወደሚል ፍልስፍና ሰዎቹን የወሰዱ ይመስላሉ። እነዚህ ለስሜት ደስ የሚሉና ውጤት የሚያመጡ የመሰሉ ልምምዶች ሁሉ ያለ አንዳች የፍተሻ ኬላ ወደ ቤተ ክርስቲያን መድረክ ወጥተው ትልቅ ስፍራ ሲይዙ ይታያሉ። የእነዚህ ዋና ምንጭም ኩረጃ ነው።

አንድ ክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት እግቢያቸው ውስጥ ይጫወታሉ። ሕፃናት ሁሉ እንደሚያደርጉት ከወላጆቻቸው ወይም ከቤተሰብ የሚያዩትን የመጫወት ልማድ አላቸው። አንድ

ቀን ሁለቱ እንዲህ ይጫወቱ ነበር፤ አንደኛ ልጅ ሌላዋን፥ ‘አሁን አንቺ ደንቆሮ ነሽና እፈውስሻለሁና እጅሽን ዘርጊ’ አለቻት። ዘረጋች። ጆሮ ግንድዋን ይዛ ‘ተከፈቺ!’ እያለች ደጋግማ ከጮኸች በኋላ ‘ተፈውሰሻል!’ አለቻት። ቀጥሎ፥ ‘አሁን ደግሞ አጋንንት አለብሽና አወጣልሻለሁ’ አለች። ሌላዋም እሺ አለች። ‘ውጣ!’ እያለች ቆይታ ‘ወጥቶልሻል!’ አለቻት። ከዚያም፥ ‘በይ አሁን ደግሞ በሌላ ቋንቋ እንናገራለን፥ እኔ እጄን ስጭንብሽ እንደኔ ትያለሽ’ አለችና እጅዋን ስትጭንባት ሁለቱም፥ ‘ሞኮሮኒ፥ ሞኮሮኒ፥ ሞኮሮኒ፥ ሞኮሮኒ’ እያሉ መዝለል ጀመሩ። ይህ የተፈጸመ የልጆች ታሪክ ብቻ ነው። ግን ከዚህ ያላነሰ ነገር አዋቂዎችም ሲያደርጉ ለማየት ሩቅ መሄድ የለብንም። ልምምድና ኩረጃ ለብዙ ነገሮች በጤናማ ሁኔታ ሊያገለግሉ የሚችሉ ነገሮች ቢሆኑም በጸጋ ስጦታዎችና በአገልግሎት ጥሪ ዘንድ ከተደረጉ አደጋ ይፈጥራሉ። መንገድን ሳይሆን ውጤትን ብቻ ማየት፥ ‘እንዴት ሆነ?’ ከማለት ይልቅ ‘ምን ሆነ፥ ምን ተፈጸመ?’ ብቻ ማለትም ጥበብ አይደለም። ሲያስተምሩም የኢየሱስን ስም ወይም መንፈስ ቅዱስን ደጋግመው መጥራትና አንድ ጥቅስ ከዚህ ሌላውን ከዚያ መጥቀስ እነዚህ ነገሮች ልምምዱን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አያደርጉትም።

6፥ *ከወንጌል ስርጭት ይልቅ የሌሎች ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንን መዝረፍ።* በወንጌል ስርጭት የሚተጉ ማኅበራት መኖራቸው እሙን ነው። በአብዛኛው ግን የካሪዝማዊ ንቅናቄ ዋና የዕድገት ስልት ወንጌልን ወዳልዳኑት በማሰራጨት ሳይሆን የዳኑትን በመጥለፍና በመገየር ወይም ምዕመናንን ከአንድ ጎተራ ወደ ሌላው በመገልበጥ ነው። ይህን ቀደም ሲል የአኩራፊዎች ጉባኤ በሚል ንዑስ ርዕስ ስር አይተናል። እነዚህ ማኅበራት ብዙውን ጊዜ ከነባር አብያተ ክርስቲያናት በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ቅር ተሰኝተው እዳር ያሉ፥ ወይም መንፈሳዊ ብስለት የጎደላቸውን፥ ወይም በቀላሉ አማኝና የዋህ የሆኑ ክርስቲያኖችን የሚሰበስቡ ናቸው።

7፥ *የሌሎች ሃይማኖቶች ትምህርቶችን ክርስትና አስነስቶ መውሰድ።* ሌሎች ክርስቲያናዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶች ከሚያስተምሩአቸው ውስጥ ለሥጋዊ አእምሮና ለስሜት ጥሩ መስለው የታዩ ትምህርቶች ከተገኙ መውሰድ ሌላው ባህርይ ነው። አሳቦቹን ወስዶ ወደ እነዚያ ትምህርቶች የሚቀርቡ ጥቅሶችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምንም ፈልጎ በላያቸው በመደረት ክርስቲያናዊ አስተምህሮ አስመስሎ ወደ ቤተ ክርስቲያን ማስገባት የቆየ ልምድ ሆኖአል። ከዚህ ክፍለ ዘመን መግቢያ ቀደም ሲል ጀምሮ አንዳንድ ዲበ አካላዊ የስሕተት ትምህርቶች ሕመም የሌለ ነገርና በሰው አእምሮ ውስጥ ብቻ የሚፈጠር ቅዠት መሆኑን እንዲሁም ሞትም መዘለልና መታለፍ የሚችል ክስተት እንደሆነ





ያስተምሩ ነበር። ይህን ትምህርት አንዳንድ ክርስቲያን አስተማሪዎችም ተቀብለው እንዳይጠፋ ሲያራግቡት ቆይተዋል። እንደ ኤልያስ እነጠቃለሁ እንጂ አልሞትም የሚል አንድ ሰውም አጋጥሞኛል። ሰዎቻቸው ሲታመሙ እንዳልታመሙ እንዲቆጥሩና ከሞቱም እንዲነሡ የትንሳኤ ሥርዓተ ጸሎት ያደረጉ ጉባኤዎች ጥቂት አልነበሩም።

በ1980ዎቹ አጋማሽ በአዋሳ ‘የክብሩ ወንጌል’ የሚባል አንድ ቤተ ክርስቲያን ተመሥርቶ ነበር። በዚህ ጉባኤ ከነበሩት ከእውነት የሸሹ ትምህርቶች አንዱ ‘ክርስቲያን መሞት የለበትም’ የሚል ነበር። መሪዎቹ ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ሰዎችን ፈልፍለው ከወሰዱ በኋላ ለጥቂት ወራት ሲያመልኩ ቆዩ። አንድ ቀን የጉባኤው መሪ የነበረ ሰው ጥቁር ውኃ ከሚባለው ፍተሻ ኬላ ላይ ተያዘ። የፍተሻ ኬላው የኮንትሮባንድ ሸቀጦችና ቡና የሚፈተሽበት ሲሆን ይህ ሰው ሁለቱንም አልያዘም። ሰውየው የያዘው በጆንያ ውስጥ የተጠቀለለ የገዛ ሕፃን ልጁ በድን አካል ነበር። ‘ክርስቲያን አይሞትም’ ብሎ የሚያስተምረው ሰው ቤት ውስጥ ሞት ሲገባና ልጁን ሲወስድ ትምህርቱንና ጉባኤውን በሕይወት ለማቆየት ሲል ልጁን በድብቅ ወስዶ ለመቅበር ባደረገው ሙከራ መሃል ተያዘ። ይህ የአለመሞት ትምህርት ቀደም ሲል በ1960ዎቹ ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥ የታወቀ ነበር። ትምህርቱ የተጀመረው ፍራንክሊን ሆል በተባለ አሜሪካዊ ነው። ፍራንክሊን በፈረንጆች አቆጣጠር በ1940ዎቹና 1950ዎቹ የገነነ በጾምና ጸሎት ላይ ትልልቅ ትምህርትና ስልጠናዎች ይሰጥ የነበረ አስተማሪ ነው። 1950ዎቹ ዘመናዊው ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ስር የሰደደበት መሆኑ ይታወቃል። የፍራንክሊን ትኩረት ጾም ሲሆን ጾም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጠቃሚና ትክክለኛ የጸሎት ሕይወት አጋር ነው። ነገር ግን ይህ ሰው ጾም በራሱ ኃይል እንዳለው በፈረንጆች አቆጣጠር በ1946 የጻፈውና ያሰራጨው የተሳሳተ ትምህርት በሰፊው ተቀባይነት አግኝቶ ነበር።[26] ፍራንክሊን ጾም አለመሞት ጨምሮ ምድራዊ ችግሮችን ሁሉ እንደሚያስወግድ ሲያስተምር እንግዳ ትምህርቶችንም ጭምር ያስተምር ነበር። ለምሳሌ፥ ለተፈጥሮ ሕግጋት እንቢ ማለትን፥ ክብደትን አጥፍቶና ከምድር ስበት ሕግ ነጻ ሆኖ መንሳፈፍ እንደሚቻልም ጽፎአል። ልብስና ጫማም ማርጀት እንደሌለባቸው አጠንክሮ አስተምሮአል። ስለ ጾም ሲያትት ይህ ልምምድ ሞትን ራሱንም እንደሚያሸንፍ በሌላ መጽሐፉ ሲጽፍ እንዲህ ብሎአል፤ “የእግዚአብሔር ቃል ስንፈጽመው የጽድቅን ዝናብ ያወርዳል፤ ብዙ ነቢያት በትንቢቶቻቸው የተናገሩትን የኢመዋቲነት ወይም

---

[26] Hall, p.19.

ያለመሞትን (immortality) ዝናብ በምድር ላይ ያወርዳል።"[27] ራሱ ፍራንክሊን የኢመዋቲነትን እርከን ማለፉንም አውጆአል።

አለመታመምና አለመሞት ለሰው ስሜት ስለሚመቹ ብቻ ተመርጠው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይኖሩም ከሆነ ተቀራራቢ ጥቅስ ጋር ተጣብቀው፥ ክርስቲያን ሳይሆኑ ክርስትና ተነሥተው ወደ ቤተ ክርስቲያን የገቡ የትሮይ ፈረሶች ናቸው። ክርስትና በአማኝና በክርስቶስ መካከል ባለ የእውቀትና የእምነት ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ሕይወት እንጂ በተወሰነ ቀን ክርስትና ስለተነሡ ክርስቲያን እንደማይሆኑ ሁሉ እነዚህ ትምህርቶችና ልምምዶችም ክርስቲያናዊ ስም ስለሰጠናቸው ወይም ከአንድና ሁለት ጥቅሶች ጋር ጀርባ ለጀርባ ስላጣበቅናቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊሆኑ አይችሉም።

*8፥ <u>ተአምራትንና ምልክቶችን ከልክ ያለፈ መራብና መጠማት</u>።* ተአምራት ለመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ለክርስትና ታሪክ እንግዳ ባይሆኑም በእያንዳንዱ ጉባኤ ውስጥ ተአምር ከተፈጸመ እንደ እግዚአብሔር መገኘት፥ ይህ ካልሆነ ደግሞ እግዚአብሔር በዚያ ጉባዔ እንዳልኖረ መቁጠር ስሕተት ነው። ተአምር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸም እንጂ እኛ በፈለግንበት ጊዜና ቦታ እንደ ክብሪት የምንጭረው ትንሽ ነገር አይደለም። የተአምራት ናፍቆት የካሪዝማዊ እንቅስቃሴ አንድ መዘዘኛ ባህርይ ነው። መዘንጋት የሌለበትና እንድንጠነቀቅ የሚጋብዘን ሌላ ነጥብ ተምራት ሁሌም በእግዚአብሔር ብቻ የማይደረጉ መሆአቸው ነው። ተአምራት በሰይጣንም፥ በተለይ በዘመኑ መጨረሻ የሚደረጉ መሆና ቸው በቃሉ ተጽፎአል። የክርስቲያን የምልክት ጥማትና የሰይጣን የማታለል ሥራ በመንገድ የተገናኙ ዕለት የሚፈጸመው አደጋ ቀላል አይሆንም። የሰይጣን ተአምርና የእግዚአብሔር ተአምር ከውጪ ሲታዩ መልካቸው ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል። ግን ፈጽሞ የተለያዩ ነገሮች ናቸው።

በዚህ ንቅናቄ ውስጥ ተአምራት የየቀኑ ክስተት እንደሆኑ ተደርገው ነው የሚነገሩት። እያንዳንዱ ምዕመን ከአንድ ተአምር ወደ ሌላ እየተሻገረ እንደሚኖር ነው የሚነገሩት። ነገር ግን እነዚህን ተአምራት የተባሉ ነገሮችና በመጽሐፍ ቅዱስ ተአምር ተብለው የተጠቀሱትን ነገሮች ስናስተያይ ምንነታቸውን መረዳት አያዳግትም።

ተአምራት ቢከሰቱም ሁሌም ከእግዚአብሔር ናቸው ብሎ መቀበል የዋኅነት ነው። እንዲህ ከሆነ የሰይጣን የማስመሰል ሥራ ወዴት አለ? የደርግ መንግሥት እንደወደቀ ጸጥታ ከመረጋጋቱና የኢሕአዴግ መንግሥትም ከመጠናከሩ በፊት በተለያዩ ቦታዎች

---

[27] Hall, *The Return...* p. 2-3.





ጊዜያዊ ረብሻና ዘረፋ ሆኖ ነበር። ሰዎችም በተለያዩ ምክንያቶች ሞተዋል። በጊዜው በአገር ውስጥ አልነበርኩም፤ ግን ይህ ከሆነ ከአንድ ዓመት በኋላ ወዳደግኩበት አካባቢ ሄጄ ሳለሁ በአንድ መንደር የነበሩ በርካታ ቤተ ሰቦች መሞታቸውን ሰማሁ። ምን ዓይነት ወረርሽኝ እንደፈጃቸው ስጠይቅ ወረርሽኝ አለመሆኑን ነገሩኝ። ጸጥታ ጠፍቶ ሁሉ ረብሻና ዘረፋ በሆነበት በዚያ ጊዜ በአካባቢው ከነበሩት ሰዎች ጥቂቶቹ ወደ ቀበሌው ገበሬ ማህበር መጋዘን በመግባት ነጭ የፉርኖ ዱቄት በማዳበሪያ ከረጢቶች ተከምሮ ያገኛሉ። ግማሾቹ በትከሻቸው ሌሎቹም በአጋሰሶች ጭነው ወደ ቤታቸው ተመልሰው ይህን ዱቄት አንዳንዱ ቤተ ሰብ አገንፍተው ሌሎቹ ጋግረው በልተው አደሩ። የበሉት ሁሉ በጊዜው የከፋ ሕመም አልተሰማቸውም። በማግስቱ ግን ሁሉም ሞተው ነበር የተገኙት። እነዚህ ሰዎች የበሉት የፉርኖ ዱቄት ሳይሆን ያንን የሚመስል በጊዜው ለገበሬዎች ሊታደል የመጣ ዳፕ የሚባል የአፈር ማዳበሪያ ነበር። ነጭ ዱቄት ሁሉ የፉርኖ ዱቄት አይደለም። ተአምራትም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተደረጉ ተአምራት አይደሉምና እንጠንቀቅ።

በካሪዝማዊ እንቅስቃሴና አሁን በሪቫይቫልና ተሐድሶ ስም እየታወቁ በመጡ ንቅናቄዎች ውስጥ ጉልህ ስፍራ የያዘ ሊያስታግሱት የማይችሉት የምልክት ወይም የትእይንት ረሃብ አለ። ምልክት ወይም ትእይንት ያልኩት በሌሎች ምሑራንም ሆነ በንቅናቄዎቹ በራሳቸው ዘንድ *manifestation* የሚባለውን ነው። ትእይንት ብዙውን ጊዜ የሚታዩ ነገሮችን ብቻ የሚወክል ቃል በመሆን ሊጠብብ ይችላል። *manifestation* በአጠቃላይ በንቅናቄው ልምምድ የሚታዩ ነገሮችን፥ የሚሰሙ ድምጾችን፥ አካላዊ እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ክስተቶችንም ይጠቀልላል። ቀደም ባሉት የጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴና ካሪዝማዊ ንቅናቄዎች ዓመታት በልሳኖች ከመናገር ቀጥሎ መወራጨት፥ መንቀጥቀጥ፥ መግዘፍና መገንደስ ነበር ብዙ የሚታወቁት። እነዚህ ልምምዶችና ትእይንቶች በየጊዜው ይለዋወጣሉ፤ በባህርያቸውም ልምምዳዊ ስለሆኑ አንዱ ሲከስም ሌላ ይተካል። በቶሮንቶው ንቅናቄ አማካይነት የተዛመተው ቅዱስ ሳቅና ቅዱስ ጩኸት ነበር። ከሳቅና ጩኸቱ ጋር ተያይዞ እንደ አራዊት ማጓራትና እንደ ሠራዊት ማቅራራት *(animal noises and war cries)*፥ እንደ ሰካራም መንገዳገድ *(acting drunk)*፥ ጦር እንደሚወረውሩ ወይም በሰይፍ እንደሚቆርጡ እጅ ማወናጨፍ፥ በቡጢ እንደሚመቱ መሰንዘር ወይም እንደተመቱ ሆኖ የተመቱበትን ቦታ ይዞ ኩምሽሽ ማለት *(doing crunches)*፥ እንደምትወልድ ሴት ኀንበስ ወይም በርከክ ብሎ ማማጥ *(birthing)*፥ ወዘተ ጥቂቶቹ ናቸው። አካላዊ እንቅስቃሴ ከሌለባቸው ክስተቶች መካከል የወርቅ ጥርስና የወርቅ ብናኝ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተሰሙ ትንግርቶች ነበሩ። የወርቅ ጥርስ ተሞላን የሚሉ ጥቂት ያልሆኑ ሰዎች ወደ አደባባይ ወጥተዋል፤

በአገራችንም ተሰምቶአል። የተመረመሩት ሰዎች ምስክርነትና የጥርስ ሐኪሞቻቸው መረጃ ግን የማይስማማ ሆኖ ተገኝቶአል።

የወርቅ ብናኝ ወይም የወርቅ ዱቄት የተባለውም ሌላው ትንግርት ሆኖ ባለፉት ዓመታት ሲወራ ቆይቶአል። ታሪኩ እንደ ፈረንጆች ቆጠራ በ1990ዎቹ መጨረሻ በካሪዝማውያን ዘንድ የተዛመተ ትንግርት ነው። ሲልቫኒያ ማቻዶ የተባለች ከብራዚል የሆነች ወንጌላዊት ከእጅዋና ከመጽሐፍ ቅዱስዋ የሚፈስ የወርቅ ዱቄት መኖሩ ይነገራል። ብዙዎች ይህን የሚያብለጨልጭ ብናኝ አይተዋል፥ ተአምርነቱንም አምነዋል። በ1999 ይህ ነገር አወዛጋቢ እየሆነ ሲመጣ *ካሪዝማ* የተባለው የአሜሪካ ጴንጤቆስጣዊ መጽሔት ዝግጅት ክፍል ናሙና ብናኞችን በዋሺንግተን ዲሲ ወደሚገኘው የዩ ኤስ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ቢሮ በመላክ መልስ ይጠብቃል። የምርመራው ውጤት ብናኙ ምንም የወርቅ፥ የብር ወይም የፕላቲነም ብናኝ የሌለውና ግን የሚብለጨለጭ የፕላስቲክ ዱቄት ወይም ብናኝ ብቻ መሆኑን አረጋገጠ። የ*ካሪዝማ* መጽሔት ራሱ ይህን የማጣራት ሥራ ማድረጉና በመጽሔቱ ማውጣቱ አስመስጋኝ ነው።[28] ይህ 'ያብለጨለጨ ሁሉ ወርቅ አይደለም' የሚለው ብሂል ለትንግርቱ ብቻ ሳይሆን ለትምህርቱም እንዲሆን የሚጋብዝ አጋጣሚ ነው። ነገሩ ተመርምሮ የወርቅ ብናኝ አለመሆኑ ተረጋገጠ እንጂ እውነት ወርቅ ቢሆንስ? ጥቅሙ ምንድርነው? ሰብስበው ጌጥ ወይም ሸጠው ቤተ ክርስቲያን ይሠሩበት ይሆን? ካልሆነ ይህ ከዚህ ትምግርት ጀርባ ተአምር የሚሠራ ኃይል መኖሩን በግልጽ ያሳየናል። እንደ ክርስትና ትምህርት ደግሞ ተአምራትን *መሥራት የሚችሉ ሁለት ብቻ ናቸው፤ እግዚአብሔርና አጋንንት።* ተአምሩ ወይም ትንግርቱ ወይም ትእይንቱ የሰውን አትኩረት ከቃሉ እውነት ወደ ነገሩ ብቻ የሚስብ ከሆነ ይህ ከእግዚአብሔር አይደለም። በእኔ ግምት በቀላሉ እንደምንማረክና እንደማንማረክ ሰይጣን በትንሹ እየፈተሸን፥ እየሞከረን ያለ ይመስለኛል።

*9፥ <u>ለጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ወይም ዶክትሪን ተገቢ ስፍራን አለመስጠት</u>።* አምልኮና ጸሎት የክርስትና ሕይወት ክፍሎች ናቸው እንጂ ብቸኛና ዋና መሠረቶች አይደሉም። ጠንካራ አስተምህሮዎችን ቃል፥ ዶክትሪን፥ ፊደል እያሉ ማጥላላት ወደ ስሕተት የመድረሻ አቋራጭ መንገድ ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለትምህርቱ እንዲጠነቀቅ ነው የነገረው፤ የመጀመሪያዎቹ ምዕመናንም ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ በሐዋርያት ትምህርትም ይተጉ ነበር፤ ሐዋ. 2፥42፤ 1ጢሞ. 4፥16።

*10፥ <u>ፈጽሞ በቃሉ የሌሉ ነገሮችን እንደተጻፉ አድርጎ ማስተማር</u>።* ውሸት ተደጋግሞ ሲነገር እውነት ባይሆንም እውነትን

[28] Charisma News, Sep. 9, '99





ግን ይመስላል ተቀባይነትም ያገኛል። አንዳንድ ክርስቲያኖች የሚሰሙት ነገር ሁሉ እውነት የሚመስላቸውና ሰባኪዎች የሚሉትንም ነገር ሁሉ ያለ ምንም ጥያቄ የሚቀበሉ፥ በቀላሉም የሚያምኑ ናቸው። ስለዚህ በቀላሉ ለመወናበድ የተመቻቹ ናቸው። በተለይ አንዳንድ አገልጋዮች ታዋቂነታቸውና የመድረክ ሰውነታቸው ለእነርሱ ተደናቂነትንና ለሚናገሩት ሁሉ ደግሞ ያለ ገደብ ተቀባይነትን ያተርፍላቸዋል።

አንድ በጣም እውቅ የሆነ አገልጋይ በአንድ የአገልጋዮች ስልጠና ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲያስተምር ስለ ቅባት ሰፋ ያለ ትንታኔ ሰጠ። ስለ ቅባት ያስተማረው ትምህርት ጭብጥ ሁለት ዓይነት ቅባቶች መኖራቸውንና አንዱ የደኅንነት ሌላው የአገልግሎት መሆናቸውን ነው። ለማስረጃ የቀረቡ ጥቅሶች ግን ፈጽሞ አልነበሩም። በአጋጣሚ ከእርሱ ትምህርት ቀጥሎ የተሰጠው ትምህርት ስለ ዘመኑ የስሕተት ትምህርቶችና ልምምዶች ሆኖ አንዱ ንዑስ ነጥብ በቃሉ ውስጥ ያልተጻፉ ትምህርቶችን እንደተጻፉ ያህል ቆጥረው ስለሚያስተምሩ ሰዎች ልምምድ ሁኔታ ነበር። ስለዚህ ይህ 'ሁለት ዓይነት ቅባት' የሚባለው ትምህርት ራሱ እንደምሳሌ ሆኖ ተወሳና እንዲህ ያሉ በቃሉ ውስጥ ከቶ የማይገኙ ትምህርቶች እንዳሉ ተደርገው እንደሚስተማሩ ተነገረ። በመጽሐፍ ቅዱሳችን እንዲህ የደኅንነትና የአገልግሎት ተብሎ የተሸነሸነ ቅባትን አናገኝም።[29] ነገር ግን ከአገልጋዩ ተደማጭነት የተነሣ ብዙዎች ተሳታፊዎች ትምህርቱን ያለምንም ጥያቄ ነበር የጎረሱት። ይህ ብቻ ሳይሆን ይህ ትምህርት ስሕተት መሆኑን የተናገረውን የኋለኛውን አስተማሪ የወረፉ ጥቂቶችም ነበሩ። ከአንዳንድ አገልጋዮች ስለ ቅባትም ሆነ ስለመሳሰሉት ነገሮች የምንሰማው የተጣረሱ ብቻ ሳይሆኑ በቃሉ ውስጥ ፈጽመው የማይገኙ ትምህርቶች ናቸው። ሰባኪዎቹም ከሌላ ሰባኪዎች ወይም መጻሕፍት እንደሰሙና እንዳነበቡ፥ እንደመሰላቸውና በጊዜውም እንደመጣላቸው የሚናገሩአቸው ነገሮች ናቸው። በቃሉ የማይገኝንና የተሳሳተ ነገርን መናገራቸው በአንዳንዶቹ ዘንድ ሆን ብሎ ለማሳሳት የታለመ ላይሆን ይችላል። ባይሆንም ግን ማሳሳቱ አይቀርም።

በፈረንጆች በ1704 በለንደን በጣሙን ታዋቂ የሆነ ጆርጅ ሳልማናዘር የተባለ ሰው ነበረ። ጆርጅ እጅግ የተማረ የፎርሞሳ ተወላጅ መሆኑን በመናገር ተዋወቀ። በዘመኑ ፎርሞሳ ብዙም የምትታወቅ አገር አልነበረችም። ከዚያ በኋላ ጆርጅ ስለ ፎርሞሳ፥ ስለ ሕዝቡ ቋንቋ፥ ስለ ባህሉ፥ ስለ አገሪቱ መልክዓ ምድር በሰፊው አስተማረ። ትልልቅ መጻሕፍትም ጻፈና በእንግሊዛውያን

[29] ስለዚህ ነጥብ በዝርዝር ለመረዳት *በመንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች* ገጽ 162 እስከ 170 ድረስ ተመልከቱ።

ዘንድ በጊዜው ታላላቅ ምሑራን የሚያገኙትን ያህል ተቀባይነት ተቀዳጀ። ከአያሌ ዓመታት በኋላ ግን ጆርጅ የተናገረውና የጻፈው ሁሉ ነገር ምንም እውነትነት የሌለውና ራሱ የፈጠረው መሆኑን፥ እርሱም ራሱ የፎርሞሳ ተወላጅ ሳይሆን ፈረንሳዊ መሆኑን እየተጸጸተ ተናዝዞ ተናገረ። ያስተማራቸው ትምህርቶችና የጻፋቸው መጻሕፍት በሕዝቡ ዘንድ ትልቅ አመኔታ ስላሰጠው ውሸታም መሆኑን በተናገረ ጊዜ የሰሙት ሰዎች ሊያምኑት አልቻሉም። እንዲያውም ትንሽ የቀወሰ ወይም ከፊት ይልቅ አሁን ሊያታልላቸው እየሞከረ ያለ መሰላቸው። ውሸቱን እውነት አድርገው ስለተቀበሉት እውነተኛውን እውነት ሲናገር ሊቀበሉት አልቻሉም።

ጂም ቤከር በመጽሐፉ 'ተሳስቼ ነበር' ባለበት ምዕራፍ ውስጥ ከጻፋቸው ነገሮች አንዱ በወኅኒ ሳለ እዚያ ለነበሩ አንዳንድ ክርስቲያኖች ቀድሞ ያስተማራቸው ትምህርቶች የተሳሳቱ መሆና ቸውን ሲናገር ጥቂቶቹ ይደናገጡና በጥያቄም ይዋጡ ነበር። አንዳንዶቹም የቀድሞውን ትምህርቱን እውነትነት ከልብ ከማመና ቸው የተነሣ አሁን የሚናዘዘውን ንስሃ እንደ እውነት መቀበል ይከብዳቸውም ነበር። ለእነዚህ ሰዎች የመለሰላቸው መልስ፥ "በዚያን ጊዜ ያስተማርኩት ነገር እውነት መሆኑን በሙሉ ልቤ አምን ነበር፤ ይሁን እንጂ በሙሉ ልቤ ግን ተሳስቼ ነበር። አንድ ሰው አንድን ነገር ብዙ ጊዜ ደጋግሞ ወይም ጮኾ መናገሩ ያንን ነገር እውነት አያደርገውም። ትልቁ ጥያቄ 'የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል?' የሚለው ነው" በማለት ነበር።[30] እውነት ነው፤ በቃሉ ያልተጻፈ ማናቸውም ነገር ተደጋግሞ ስለተነገረ እውነት ሊመስል ቢችልም እውነት ግን አይሆንም።

የአንዳንድ ካሪዝማውያን ሰባኪዎች ያልተጻፈውን የመስበክ ሌላ ችግር እግዚአብሔር ወይም መልአክ ተገልጦ፥ ወይም በራእይና ሕልም የታያቸውን ወይም በምናባቸው ተከስቶ ያሰላሰሉትን ሥልጣን እንዳለው ሁሉ አድርገው ሊያቀርቡና ሌሎችም እንዲቀበሉት ሊያደርጉ መጣራቸው ነው። ይህም ሌላ ስሕተት ነው። እግዚአብሔር እንደዚህ ያሉ ነገሮችን ጨርሶውኑ አይሠራም ማለት አይደለም፤ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ወዲህ የሆኑ ነገሮች ናቸውና የትምህርትም ሆነ የኑሮ ሥልጣን ሊኖራቸው አይችልም። በቃሉ ውስጥ የማይገኝ አዲስ መገለጥ ከቶ የለም። በቃሉ ውስጥ ያለው ደግሞ ሙሉ ከሆነ ለአዲስ መገለጥ ቦታ አይኖርም። ሥልጣን ያለው አዲስ መገለጥ ከኖረ ቃሉ ሙሉ አይደለም ማለት ነው። እንደገና ለማስመር፥ በቃሉ ያልተጻፈ ማና ቸውም ነገር ተደጋግሞ ስለተነገረ እውነት ሊመስል ቢችልም

30 Bakker, p.535.





እውነት ግን አይሆንም። እነዚህን መሳይ በርካታ ችግሮች ዋና ምንጭ ሰባኪዎቹ መገለጥ ወይም የመገለጥ እውቀት *revelation, revelation knowledge* የሚሉት ነው። አንዳንዶች ባለማስተዋልና ምንነቱን በውል ሳያውቁት ቃሉን ቢጠቀሙበትም፥ ይህን ቃል የሚጠቀሙበት ሰባኪዎች ብዙውን ጊዜ የማንነታቸው መታወቂያ አድርጎ ለማሳየት ነው። እግዚአብሔር ሥልጣን ያለውን ቃሉን ለመጀመሪያዎቹ ጸሐፊዎች ከሰጠበት ወይም ከገለጠበት ባላነሰ ሁኔታ ለእነርሱም እንደገለጠላቸው ሳይፈሩ ይናገራሉ። እንዲህ ያሉ ሰባኪዎችን ከሰማን እጅግ ልንጠነቀቅ ይገባናል፤ ምክንያቱም ተገለጠልን ብለው የሚያደርጉት ወይም የሚናገሩት ነገር ግልጽ ከሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚጋጭ ነው። እንዲህ ያሉ መገለጦች ደህና ከተባሉ የሰው ግምቶችና አስተያየቶች፥ ከከፉ ደግሞ ጭልጥ ያሉ የስሕተት ትምህርቶች ናቸው።

# *የተስፋ ሻሞ*

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ የተስፋ ቃሎች ተጽፈዋል። እግዚአብሔር ተስፋን የሚሰጥና የሰጠውንም ተስፋ የሚፈጽም አምላክ ነው። የተስፋ ቃሎች ይጻፉ እንጂ የተጻፈው ሁሉ ያለገደብ የኛ ነው ማለት አይደለም። ይህ አሳብ በስነ ትርጓሜ ምዕራፍ በተለያዩ ቦታዎች ተጽፎበታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለተነገረላቸው ሰዎች የተሰጡ ተስፋዎች እንዳሉ ሁሉ ያለፉትንና የዚህንም ዘመናት አማኞች የተመለከቱና ለእነርሱ የተሰጡ ተስፋዎች አሉ።

*የእግዚአብሔር ተስፋዎች መጽሐፍ* የሚባል አንድ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ የተጻፉትን ተስፋዎች በሙሉ ለቃቅሞ ይዞአል። በመግቢያው ላይ በውስጡ የተጻፉትን ተስፋዎች በየቀኑ የተወሰኑትን በማንበብ አንባቢው ለራሴ ብሎ እንዲወስድ ይጋብዛል። ልክ ለየቀኑ ብሎ ሐኪም እንደሚያዘው ኪኒን። እኛን የሚመለከቱትን የተስፋ ቃላት ማወቅና የኔ ብሎ መውሰድ፥ በተስፋ ሰጪውም ታምኖ መሰማራት ተገቢ ነገር ነው። የኛ ያልሆነውን ሁሉ ግን ልጆች ሆነን እንደምናደርገው ሻሞ ተብሎ ወደላይ እንደተበተነ ከረሜላ ወይም ሌላ ነገር ተሻምተን ለመውሰድ መታገል ሌላ ሳይሆን ትግል ብቻ ነው። እግዚአብሔር የተስፋ ርችት ተኳሽ ባለ ነፍጥ አይደለም። ለሰዎች በቀጥታም ሆነ በነቢያቱ አማካይነት ሲናገር ምንን ለማን እንደሚናገር ያውቃል። የተናገረውንም ፈጽሟል፥ ይፈጽማልም።

ተስፋዎች ጥሩ ነገሮች ናቸው፤ ለመስማት ይጥማሉ። መስኅብነት አላቸው። በተሳሳተ ልማድ ግን የተጻፈውን ተስፋ ሁሉ

የኛ አድርገን ልንወስደው ይከጅለናል እንጂ ተስፋ ሁሉ ለእኛ አይደለም። በተለይ እንዲህ ያሉ የተስፋ ስብከቶችን የሚሰብኩ አንዳንድ ሰባኪዎች ጉም ሲያስዘግኑ የሚያኖሩ ናቸው። አንዳንዶቹ ካለመረዳትና የተሳሳተ ስነ ትርጓሜ የተነሣ የሚደርሱበት ድምዳሜ ሲሆን አንዳንዶቹ ግን ለራሳቸው ብልጽግና ልክ መዥገር የከብቶችን ለስላሳ ቆዳ ፈልጎ ተጣብቆ ደማቸውን እንደሚመጥ የሌሎችን ንዋይ ለመምጠጥ በለስላሳ የተስፋ ቃላት መደለያነት መጠቀማቸው ነው። አንዳንድ ሰባኪዎች ብቻ ሳይሆኑ ብዙዎቹ ዘማሪዎቻችን የሚዘምሩት መዝሙርም ይህን መሳይ ነው። እነርሱ ደግሞ ተስፋውን የራስ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን እንደ ባለተስፋዎቹ አድርገውም ነው የሚዘምሩት። ዳዊትም ኤልያስም እነሱ፥ ኢያሱም ጌዴዎንም እነሱ፥ መርዶክዮስም ጳውሎስም እነሱ፥ ሳራም ኤልሳቤጥም በርጠሜዎስም 12 ዓመት ደም የፈሰሳቸውም እነሱ፥ ለነዚህ የተባለውም ለነሱ የተባለ፥ ተስፋውም በነሱ የተፈጸመ ይመስላል።

በቃሉ ውስጥ ካሉት የተስፋ ቃላት በመነሣት የተስፋ ሰጪውን ባህርይ በማወቅ በእርሱ መታመን አንድ ነገር ነው፤ ለኛ ያላለውን ግን እንዳለ አድርገን መቁጠር በእጁ ውስጥ ለኛ ያልያዘውን ነገር ለመውሰድ እጁን እንደመፈልቀቅ ከንቱ ትግል ነው። እንዲያው ቢሆንልንና ፈልቅቀን ብንከፍት እንኳን ያ ተስፋ የለበትም። ተስፋ ሰጪው አምላክ ለሰዎቹ ከሰጠው ተስፋ በመነሣት ያ እንደዚያ ያደረገው አምላክ አልተለወጠም ብሎ በእርሱ መታመን አንድ ነገር ነው፤ ግን ብኋልና ማድረግ አለበት ብሎ ማስገደድ የኋላ ኋላ ወደ ቅሬታ ውስጥ ይጥለናል። አንድ ሰባኪ ስለ ብልጽግና ሲሰብክ ዋና ጥቅስ ተደርጎ የተወሰደው ዘፍ. 12፥2-3 ነበር። ያ ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ ሁሉ ቃል በቃል ለእኛም ነው በማለት ረጅም ሰብከት ተሰበከ። እንግዲህ ቃል በቃል ያ ተስፋ ለእኛም ከሆነ በቁጥር 1 እንደተጻፈው ከዘመዶቻችንና ከአባቶቻችን ቤት ወጥተን ወደሚያሳየን ምድር መሄድንም ቃል በቃል ወስደን መሰደድ ሊኖርብን ነው። እንዲህ ለኢያሱም፥ ለእስራኤልም፥ በምርኮ ለነበሩ አይሁድም የተሰጠውን ሁሉ ለኛ ያደርጉታል። ሁሉ ለእኛ ግን አይደለም።

የተስፋ ችሮታን በኢትዮጵያውያን ዘንድ የግለሰብና የጉባዔ ብቻ አድርገን አንወስደውም። ኢትዮጵያውያንን በተመለከተ ትንቢትና ተስፋው ብሔራዊም ነው። 'ኢትዮጵያ' የሚለው ቃል፥ በተለይም በረከት የሚለው አሳብ በጥቅሱ አካባቢ ያለበት፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እየተፈለገ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሰማየ ሰማያት ተነድሎ የበረከት ብዛት ከስር ተነቅሎ ሊወርድላቸው በመንገድ ላይ ያለ ያስመስሉታል። አጠዳደፉንም ትልልቅ የበረከት ቁልሎች ከጸጉር በቀጠኑ አንድ አንድ ክሮች በኢትዮጵያ አናት ላይ ተንጠልጥለው ዱብ ሊሉ ምንም እንዳልቀራቸውና ምንም ነገር ያልያዛቸው አድርገው ይስሉታል።





በቅርብ የወጣ አንድ መጽሐፍ ማዕከላዊ ጭብጥ ይኸው በቅርብ በኢትዮጵያ፥ ብሎም በአፍሪቃ ቀንድ ሊፈነዳ የቀረበው ሪቫይቫል ነው።[31] ይህ ብሔራዊ ተስፋ ከመጽሐፍ ቅዱስ በተወሰደ አንድ ዋና ጥቅስና ከቅርብ ዐሠርታት ወዲህ በተነገሩ ትንቢቶች ወይም መልእክቶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቀሱት ጥቂትና፥ ለዚያውም ከዐውደ ምንባባቸው ተቆርሰውና ተከርክመው የወጡ ጥቅሶች ናቸው። ብዙውን ጊዜ እንዲህ የመሰሉ ብሔራዊ ተስፋዎችና ትንቢቶች የሚመነጩት እንደ ራእያዊ ጽሑፎች *(apocalyptic literature)* ሁሉ ዘመንና ሁኔታን ተከትለው ነው። ካሉበት ምጣኔ ኃብታዊ አዘቅትና ኋላ ቀርነት፥ ችግርና እጦት፥ ስደትና መከራ ወዘተ የሚታደግ ጌታ እንዳለና ያ ጌታም ፈጥኖ ፍትሕን ለእነርሱ፥ በቀል የሞላበት ፍርድና ቅጣትን ደግሞ በአሳዳጆቻቸው ላይ እንደሚያመጣ ከመተማመን የተነሣ የሚነገሩ የተስፋና መድፈሪያ ትንቢቶች ናቸው።

እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ከሌላው ሕዝብ ሁሉ የሚበልጥበት አንድ ሕዝብ የለውም። ያለችው አንዲት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት፤ እርስዋም የክርስቶስ አካል የሆነችው እውነተኛ አማኞችን ሁሉ የያዘችው ቤተ ክርስቲያን ናት። እንደ ሕዝብ አሜሪካውያን ከኢራቃውያን ሕዝብ ይልቅ የተወደዱ አይደሉም። ወይም እንደ አገር ፈረንሳይ ለእግዚአብሔር ከኬንያ ይልቅ የተወደደች አይደለችም። ሁሉም እኩል ናቸው እንጂ። ሌላው ቀርቶ በዚህ በቤተ ክርስቲያን ዘመን እግዚአብሔር የአሕዛብ ሙላት እስኪፈጸም ድረስ የተስፋ ቃል ያላቸውንና ሕዝቡ የተባሉትን አይሁድ እንኳ ዘመናቸው እስኪመጣ ድረስ ወደጎን አቆይቶአቸዋል። እንግዲህ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ከሌሎች ልዩ የሚያደርገን ከቶ ምን ይሆን? በእርግጥ እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ ውስጥ ሲሠራ እንደኖረው አሁንና ሁሌም ሥራውን የሚያካሂደው በተመሳሳይ መንገድ ነው። በመለኮታዊ ጣልቃ ገብነትም፥ ሌላውን ሰውና ሕዝብ በመጠቀምም። በዚህ ውስጥ አንድ ሰው፥ ማኅበር፥ ብሔር፥ ወይም አገር በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ የበለጠ ሚና ሊኖራቸው እንደሚችል የማይካድ ነገር ነው። ሆኖም ኢትዮጵያውያንን በሞኖፖል የተያዘ፥ ብቸኛና አይቀሬ የሆነ የተስፋ ባለቤት የሚያደርጋቸው የሚጨበጥ እውነት የለም። ይህ ስም 41 ጊዜ መጠቀሱ ይሆን? ሌሎችም ከዚህ እጅግ በበዛ ቁጥር ተጠቅሰዋልና ስለተጠቀሱ ብቻ የበኩር ድርሻ ይሰፈርልን ሊሉ ነው? ለምሳሌ፥ አሶር ከ120 ጊዜ በላይ፥ ባቢሎን ከ280 ጊዜ በላይ፥ ግብጽ ከ600 በላይ ጊዜ፥ ተጠቅሰዋል። የተጠቀሱት ጥቅሶች ስለምን ይናገራሉ ብሎ ዙሪያ ገባውን ማየቱ ከዚህ ስሕተት ይጠብቀናል። ወይስ በተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት

---

[31] በቀለ ወልደኪዳን፥ ገጽ 21-22፥ ወዘተ።

እኛ ኢትዮጵያውያን ዳግማዊ እስራኤል ተደርገን መመረጣችን የተወሳበትን ተውሰን ወይም በዱቤ ገዝተን እየኮራንበት ነው? ደግሞም ኢትዮጵያ የሚለው የዕብራይስጡ አቻ የሆነው ኩሽ በዚያን ጊዜ የሚወክለው አገርና ሕዝብ አሁን ኢትዮጵያ ከምትባለው አገርና ሕዝብ ምን ያህል እንደሚቀራረብ ማጤኑም ተገቢ ነው።

ከተስፋ ቃላቱ እንደ አዝማች የሚደጋገመው መዝ. 68፥31 ነው። ይህ ጥቅስ በብዙና የተለያዩ ጊዜያትና ሁኔታዎች ውስጥ የአገሪቱ ጥቅስ ሆኖ ኖሮአል። በሁለቱ የኢጣልያ ወረራዎች፥ በተለይም በሁለተኛው የመንግሥታዊ ደብዳቤዎች አርማም ነበረ። ጥቅሱ፥ "መኳንንትም ከግብጽ ይመጣሉ፤ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" ይላል። በመዝሙሩ በጠቅላላ አምልኮንና መስዋዕትን የሚገልጡ ብዙ ቃላትና አሳቦች ተዘርዝረዋል። ኃያሉ እግዚአብሔር በክብር ሲነሣና ጠላቶቹና ተቃዋሚዎቹ ሲሸነፉ፤ በአንጻሩ ደግሞ ጻድቃን ደስ ሲሰኙ የሚያሳይ መዝሙር ነው። ይህ መዝሙር የአምልኮና የምስጋና መዝሙር እንጂ ታሪካዊ ድርጊት ወይም የትንቢት ቃል ያለመሆኑ መዘንጋት የለበትም። ጥቅሱ ስለኢትዮጵያና ስለግብጽ ሲናገር እነዚህ አገሮችና የአገሮቹ ሕዝቦች ወደው ለማምለክ መፍቀዳቸውን ሳይሆን ተሸንፈው እጅ መስጠታቸውን መናገሩ ነው። ይህን አሳብ ከፊቱ ካሉት ሁለት ጥቅሶች ይበልጥ መረዳት ይቻላል። ግብጽና ኢትዮጵያ አብረው ሲሆን የተጠቀሱት ሁለቱም በመተባበር ደጋግመው አይሁድን ለመውጋት የወገኑ መንግሥታት መሆናቸው በቃሉም ተጽፎ ይገኛል። ከዚህ በላይ ደግሞ የቅርብና ሰፊ ዐውዱ ሲታይ ይህ በቅርብ ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ሊሆን ስላለው ታላቅ የበረከት መከር አይናገርም። የሆነውን ካልሆነው ለይቶ ለመረዳት ከጥቅስ ውስጥ ቃሉን ብቻ በመንጠቆ እንደሚያወጡ ከመውሰድ ይልቅ ያ ተስፋ የተሰጠበትን ስፍራ ከሙሉ አሳቡ ጋር ማጥናቱ ጠቃሚ ነው።

ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪቃንና ዓለምንም የሚያጥለቀልቅ መነቃቃትና መታደስ ከኢትዮጵያ ወይም ከየትም ቢመጣ የሚወደድ ነገር ነው። ግን የዓለማችንና የመጨረሻው ዘመን መልክ በቃሉ ተጽፎ እንደሚገኘው ከክርስቶስ ምጽዓት በፊት ያለው ጊዜ እየከፋ እንደሚሄድ ነው የሚናገረው። የመነቃቃትና የተሐድሶ ንቅናቄዎች *(Revival and Renewal Movements)* እንደሚሉት ግን የመጨረሻው ዘመን እጅግ የበዛ በረከት የሚታጨድበት ነው። ከነዚህ ትምህርቶች አንዱና *Dominin Theology* ወይም *Kingdom Now Theology* የሚባለው ቤተ ክርስቲያን ኀልብታና አይላ ዓለምን በቁጥጥርዋ ስር ሳታደርግ ክርስቶስ ፈጽሞ አይመጣም የሚል ነው። በነዚህ ንቅናቄዎችና ስነ መለኮት መሠረት ይህ ዓለምን ረትቶ በቁጥጥሩ ሥር የሚያደርገውን ሠራዊት የተገለጡት





የእግዚአብሔር ልጆች *(The Manifest Sons of God)*፥ የኢዩኤል ሠራዊት *(Joel's Army)*፥ ወዘተ እየተባሉ ይጠራሉ። ይህ ቢሆን ጥሩ ነበር፤ ግን ችግሩ እነዚህ ትምህርቶች የተመሠረቱት ከተለያዩ ቦታዎች ተወስደው እንደ ዶቃ በተደረደሩ የማይገባጠሙ ጥቅሶች ላይ መሆኑ ነው። በመጨረሻው ዘመንና ከክርስቶስ መምጣት በፊት ቤተ ክርስቲያን ዓለምን ከማጥለቅለቋ ይልቅ ዘመኑ እየከፋ፥ ክፉው እየሰለጠነ፥ የክፋት ኃይላት እየበዙ፥ የሐሰት ትምህርቶችና ሐሰተኛ ክርስቶሶችም እየበረከቱ እንደሚመጡ ነው ቃሉ የሚና ገረው። ይህ ጸለምተኝነት ሳይሆን የቃሉ ሰፊ ትምህርት ነው። የኢትዮጵያንም ወደፊታዊ 'ክርስቲያናዊ' በረከቶችና የብሔራዊ ተስፋ ብዛት ስናስብ ከዚህ ትምህርት ያልራቀ ሆኖ እናገኘዋለን። የካሪዝማዊ ንቅናቄ ስብከቶችን ተስፋ አሰጣጥና ጤናማውን የቃሉን ጥናት በስነ ትርጓሜ ምዕራፍና በናሙና ኮንፈረንስ ክፍሎች በመመልከት ማነጻጸር ይቻላል።

# የእርግማን ቀውስ

የተስፋ ልገሳ ብቻ አይደለም፤ የእርግማን ማስፈራሮ ደግሞ ሌላው የካሪዝማዊ ንቅናቄ ገጽታ ነው። *Generational Curse* ይሉታል። የዘር ማንዘር መርገም ወይም እርግማነ ትውልድ ማለት ነው። የወላጆች ወይም ያለፈው ትውልድ እርግማን በዚህ ትውልድ ያለ መሆኑን ለመግለጥ ነው። እንዲሁም አንድ ትውልድ በአንድ ምክንያት ወይም በሌላ የሚመጣበትና የሚሸከመው እርግማን እንደሚኖር ለማሳየት ነው። ትምህርቱ ክርስቲያን ወደ ክርስቶስ ሕይወት ከገባ በኋላም በእርግማን ውስጥ መኖሩ እንደማይለወጥ ያስረዳል። ዋናው ግብ ጥንቆላ በመሰለ ረቂቅ ትምህርት ሰዎችን በፍርሃትና በልቡናዊ እስራት ውስጥ ማቆየት፥ ከዚያም በኋላ ትምህርቱን ተቀብለው የተቀመሩ ቀመሮችን ሲሉ ወይም ሲያደርጉ የተፈቱ ማስመሰል ነው። ረቂቅነቱና ከዚህም ከዚያም ተወስደው የተለጠፉበት ጥቅሶች መኖር ትምህርቶችን ሳያጤኑ የሚቀበሉ ሰዎች በቀላሉ እንዲጠመዱ ያደርጋል።

ይህ ትምህርት ከክርስቶስ እምነት በኋላም ክርስቲያኖች እኛ ስናውቅ ወይም ሳናውቅ ሌሎች በእኛ ላይ የተናገሩትን ብቻ ሳይሆን በአሕዛብና በአረማዊ ሃይማኖቶች ያሉት እንደሚፈሩት መተትን፥ ጥንቆላን፥ ደንቃራን፥ አቴቴን፥ አስማትን፥ ድግምትን፥ ንግርትን፥ ሌሎችንም እጅግ የበዙ ነገሮች በመፍራትና በመሳቀቅ እንድንኖር ይዳርገናል። በተለይም አጋንንታዊ አሠራሮች በጉልህና በብዙ በሚታዩባቸው እንደኛ ባለው ኅብረተ ሰብ ዘንድ ይህ ፍርሃት ወደ ክርስቶስ በመምጣት ሊፋቅ እንደማይችል ያስመስለዋል። የዚህ ትልቅ ስሕተትም ውስብስብ ያልሆነውን

ደኅንነት ማወሳሰብና የክርስቶስን የማዳን ኃይል ዝቅ ማድረጉ ነው። ክርስቲያን ክርስቶስን ሲቀበልና ከእርሱም ጋር ሲራመድ ከሰይጣንና ከሥራው ጋር መተባበር የለበትም። ይህ ግልጽ የቃሉ ትምህርት ነው፤ ለምሳሌ፥ ያዕ. 4፥7። ነገር ግን ክርስቲያን ከሆንን እና ክርስቶስን ወደ ሕይወታችን ከጋበዝን በኋላም ሰይጣን ያለፉት ትውልዶች የሠሩትን ቆጥሮ በኛ ላይ ሥልጣኑን የሚዘረጋ መሆኑ የቃሉ ትምህርት አይደለም። ክርስቲያን ክርስቶስን ሲቀበል አዲስ ፍጥረት ሆኖአል፤ ከክርስቶስ ጋር ሞቶ ተነሥቶአል፤ በእርሱ ሆኖ ተሞልቶአል፤ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖአል፤ በእርሱ ጥበቃ ውስጥም ለዘላለም ይኖራል። ክርስቲያን በክርስቶስ ከኖረ ሰይጣን በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውም። ሰይጣን በመስቀሉ ላይ በተፈጸመው የክርስቶስ ገድል በአማኞች ላይ የነበረው አለቅነትና ባለሥልጣንነት ተገፍፎአል፥ ድልም ተነሥቶአል።

የትውልዶች እርግማን ትምህርት ከክርስትና ይልቅ ለክልዔያዊ ፍልስፍና *(Dualism)* የቀረበ ነው። በዚህ ፍልስፍና እምነት ሁለት እኩል ኃይል ያላቸው ኃይላት አሉ። ኃይላቱ አማልክትም ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ አንዱ የመልካም ሁለተኛው የክፉት ኃይላት ና ቸው። ሁለቱም ኃይላት አንዱ በሌላውና በተከታዮቹ ላይ የሚነሡሱ ሲሆኑ ይህም በተከታዮቻቸው ላይ ሊደርስ የሚችል ተጽእኖ አለው። ሰዎች የመልካም ዕድል ወይም የመጥፎ አጋጣሚ ማረፊያ ወይም ሰለባ ናቸው። ይህ ፍልስፍና በብዙ አረማዊ ሃይማኖቶች ውስጥ በግልጽ ይገኛል። አረማውያን ሃይማኖቶች አማልክትን ለማስደሰት የተለያዩ ነገሮችን ያደርጋሉ፤ ድግምት ይደግማሉ፥ ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር የተዋሃደ ቃልም ይናገራሉ። ይህን የሚያደርጉት ወይም የሚያስደርጉት ‘ዐዋቂ’ የሚባሉ ምስጢራዊ እውቀት ያላቸው ሰዎች ናቸው። የትውልድ እርግማን ትምህርትን በሚቀበሉ ካሪዝማውያን ዘንድም እንዲህ ያለ ነገር እንደሚደረግ ቀጥሎ ባሉት አንቀጾች እንመለከታለን። በክርስትና እምነት አንድ አምላክ ብቻ እንጂ ሁለት አቻ ጉልበት ያላቸው አማልክት የሉም። ሰይጣን መልአክ እንጂ አምላክ አይደለም። አምላክ ወይም ገዥ በሚል ስያሜ ቢጠራም የአምላክነት ባህርይ የለውም። ስለዚህ ከጥፋት አምልጠው ወደ እግዚአብሔር ጉያ በገቡት ላይ ከእግዚአብሔር ጋር የመከራከርና ይህን ወይም ያን እርግማን አምጥቶ በእነዚህ ሰዎች ላይ የሚከምርበት ሥልጣን የለውም። በአማኞች ላይ የይገባኛል መብት አለኝ ካለ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር እኩያ ጌታ ሊሆን ነው።

አንዳንድ ጊዜ እርግማኑ እንደበረከቱና እንደተስፋው ሁሉ ከግለሰብና ከጥቂት ቁጥር አልፎ ብሔራዊ የሚሆንበት ጊዜም አለ። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን እርግማን እንዳለባቸው የሚነገርባቸው ስብከቶችም ይደመጣሉ። አንዳንዶች ሰባኪዎች ጥቁር ሕዝብ ሁሉ የተረገመ እንደሆነ ለማሳየት ሲሉ ኩሽን የተረገመው የኖኅ ልጅ ያደርጉታል። በሚያሳዝን መልኩ ከቀድሞ ቅኝ ገዥዎች





አንሥቶ እስከዘመናዊዎቹ *Anglo-Israelism*፥ *White Supremacy, Ku-Klux-Klan* እና ወዘተ፥ የመሰሉ ክርስትናን የተላበሱ የጥላቻ ድርጅቶችና ትምህርቶች ጥቁርን ዝቅተኛ ለማድረግ ይህን ታሪክ ይጠቅሳሉ። የሚያሳፍረው ግን ይህን ያህል አጠንክረው የሚጠቅሱትን ታሪክ ከተጻፈበት ምንጭ ጠንቅቀው በማንበብ ያለመረዳታቸው ነው። ኩሽና ከነዓን ወንድማማች ሲሆኑ የተረገመው ከነዓን ነው። ከነዓን ደግሞ የጥቁሮች አባት አይደለም። ካም የአባቱን ዕርቃን ከማየቱና ከነዓንም ከመረገሙ በቀር ከነዓን ስላደረገው ነገር አናውቅም። ከላይ የተጠቀሰችው ማሪሊን ግን በመጽሐፍዋ ከነዓን በአባቱ ላይ ግብረ ሰዶም መፈጸሙን፥ ግብረ ሰዶማውያኑ የሰዶምና ገሞራ ሰዎችም የእርሱ ልጆች እንደሆኑ ጽፋለች።[32] ይህ ያልተጻፈ መገለጥ እንጂ ሌላ አይደለም። ወደ ኩሽ ስንመለስ ግን፥ ኩሽ አልተረገመም። ኢትዮጵያውያንም ከሌላው ሁሉ ሕዝብ ተለይተን የምንመረቅበት ወይም የምንረገምበት ምንም መነሻ የለም። በወል እንደ ምድር ሕዝብና አዳም ዘር ሁሉ እኛም ከሌሎች ጋር በኃጢአት ወድቀና ል። ሞትም ይጠብቀናል። እንደማንም ሰው የኃጢአት ደመወዝተኞች ነን። ከዚህ የተጨመረ ልዩ እርግማን የለብንም። በነጠላ ግን በክርስቶስ ያመነ ሁሉ ከሕግ እርግማን ተዋጅቶ የዘላለም ሕይወት ወራሽ ይሆናል።

እንደ እነዚህ ሰዎች እምነትና ትምህርት የእርግማን ዓይነቱ ብዙ ነው። በዚህ በኩል ርቀው የሄዱና ሥራ እርግማን ነው ብለው መሥራት ያቆሙ ጥቂት ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን አውቃለሁ። ይህ ‘ሊሠራ የማይወድ አይብላ’ የሚለውን ቃል የሚተላለፍ ጥሬ ስንፍና እንጂ ሌላ አይደለም። ከእነዚህ በርካቶቹ በምዕራቡ ዓለም የሚገኙ ሰዎች ናቸው። በነዚህ ባሉባቸው አገሮች ማኅበራዊ ዋስትና ወይም ደኅንነት የሚባል ሥርዓት አለ። ይህ ሥርዓት ባይሠሩም እንኳ ከመንግሥት የሚሰጣቸው ድጎማ እንዲኖር የሚያደርግ ስለሆነ ያንን እየበሉ ነው የሰነፉት። በእነዚህ ሰዎች እምነት ሥራ ከውድቀት በኋላ በነአዳም ላይ የተጣለ ቀንበር ስለሆነ የእርግማን ውጤትና እርግማን ነው። እኛ ደግሞ በክርስቶስ ያለን በእርሱ በኩል ከአዳም እርግማን ነጻ ወጥተናል ባዮች ናቸው። እውነት ሥራ እርግማን ነው? ከዔድን ገነት በፊትና በኋላ የሆነው ልዩነት ድካም መሆኑና ልፋት መብዛቱ እንጂ ሥራስ ቀድሞም በዔድን ገነትም እኮ ነበረ። ከሕግ እርግማን ወይም ኮናኝነት ነጻ መሆን የስንፍና የፈቃድ ወረቀት ነው? እንደነጳውሎስ ያሉ ብርቱ አገልጋዮች የማንም ሸክም ላለመሆን በገዛ እጃቸው ሌሊት ሌሊት እየሠሩ ቀን ቀን

---

[32] Hicky. pp. 19-20.

ማግልገላቸው ይህ የእርግማንና የነጻነት ትምህርት ስላልገባቸው ይሆን? የለም፥ ይህ ከክርስቲያናዊ የሥራ ስነ ምግባር የማይጠበቅ ቦዘኔነት ነው። ብዙዎች ምሑራን እንደሚስማሙበት የምዕራቡ ዓለም ዕድገት የተመሠረተው በክርስቲያናዊ የሥራ ወዳድነት ባህል *(Protestant Work Ethic)* ነው። ይህ ሥራ ፈትነት የዚያኛው ባህል ግልባጭ የሆነ አሳፋሪ ልማድ ነው።

ወደ ትውልዶች እርግማን ስንመለስ፥ ኒል አንደርሰን ይህንን ትምህርት አብዝቶ ያስፋፋ የታወቀ ሰው ነው። ኒል ዘጸ. 20፥4-5ን በመጥቀስ አጋንንት ከወላጆች ወደ ልጆች ብቻ ሳይሆን ከትውልድም ወደ ትውልድ እንደሚተላለፉ በመግለጥ ከቀደሙ ትውልዶች የተነሣ አጋንንት በክርስቲያኖችም ሕይወት መጫሚያና ሥልጣን እንደሚኖራቸው ያብራራል።[33] ክርስቲያኖች በዚህ እስራት ውስጥ እንዳሉ ማረጋገጥና ካረጋገጡ በኋላም "ከዘር ማንዘሬ አጋንንታዊ ሥራ እደመስሳለሁ" እያሉ ቃልን በመናገር እርግማኑን መስበር እንደሚገባ ይናገራል።[34] እንደ ኒል ትምህርት ከሆነ ክርስቲያኖች ሁሉ ይህን እውቀት አግኝተው ሰይጣንን እስኪያባርሩት ድረስ በእነርሱ ላይ ሥልጣን ይኖረዋል። መስቀሉ የድላችን መነሻ ከሆነና ከመስቀሉ ወዲህ ያለን አማኞች ገና በሰይጣን ቀንበር ስር ከሆንን ይህ እርስ በራሱ የሚቃረን ትምህርት ሊሆን ነው። ደኅንነታችን ሙሉ እንዲሆንም ከክርስቶስ እምነት ሌላ ተጨማሪ እውቀትና ቃል መናገር ካስፈለገን የክርስቶስ ሥራ በቂ አይደለም ልንል ነው። ካመንን እና ዳንን ካልን በኋላም የተባለው የመገለጥ እውቀት ኖሮን ቃልን እስክንና ገር ድረስ ገና የሰይጣን አሻንጉሊቶችና መጫወቻዎች ሆነን ልንኖር ነው ማለት ነው። አይደለም።

ከላይ የተባለው ጥቅስ ስለአጋንንትና ዲያብሎሶች አይናገርም። በክርስቲያኖች ላይ ስላላቸው ሥልጣንም አያወራም፤ ጥቅሱ የሚና ገረው የሚጠሉትንና ቃል ኪዳኑን የሚያፈርሱትን እንደሚቀጣ ነው። ቀጪው እግዚአብሔር ነው እንጂ ሰይጣን አይደለም። ተቀጪዎቹም ቃል ኪዳኑን ያፈረሱት የቃል ኪዳኑ ሰዎች ናቸው። ያ ጥቅስ የጠቅላላው የሙሴ ሕግ ወይም የሲና ተራራ ሕግጋት መግቢያ ቃል ነው። ከቶውኑ ሌሎች አማልክትን እንዳያመልኩ ማስጠንቀቂያ ነው። በተለይ ጥቅሱን እንዲሁ ስንመለከት ልጆችና ቀጣይ ትውልድ ስለወላጆችና ስላለፈው ትውልድ ቅጣት ተቀባይና ዋጋ ከፋይ እ'/ደሆኑ ያስመስላል። ይህ እንዳልሆነ በሙሴ ሕግ በሌላ ቦታ፥ እንዲሁም በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት

33 Anderson, p. 201.
34 Ibid. 203.





ማንም ስለራሱ እንጂ ስለሌላው ኃጢአት እንደማይቀጣ በግልጽ ተጽፎአል፤ ለምሳሌ፥ ዘዳ. 24፥16፤ ኤር. 31፥29-30፤ ሕዝ. 18 ወዘተ። የአባቶች ኃጢአት በልጆች ላይ ከመጣ ወይም ከተጎበኘ ልጆቹም በአባቶቻቸው መንገድ ሄደዋል ማለት ነው፤ 'በሚጠሉኝ ላይ' የሚለው ሐረግ ያንን ያሳያልና። ስለዚህ ቀጣዩ ትውልድ እንደቀዳሚው ሁሉ ከሄደ ቅጣቱ ሊያገኘው ይችላል። ያለዚያ ምንም ያላደረጉ ምስኪኖችን በመቅጣቱ እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅነቱ ሊፋለስ ይሆናል።

ከታዋቂዎቹ ካሪዝማውያን አስተማሪዎች አንድዋ ማሪሊን ሂኪ ስለዚህ ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖችም ስለሚታሰሩበት እርግማን ራሱን የቻለ መጽሐፍ ጽፋለች፤ የመጽሐፍዋ ርዕስ *Break the Generation Curse* ነው። ማሪሊን ቀድሞ በጉልህ ከምትታወቅባቸው እንግዳ ትምህርቶችዋ አንዱ ለመበልጸግ በኪስ ወይም በእጅ ቦርሳ ውስጥ የሚደረጉ ቁራጭ ጨርቆች መላኪ ነው። ከዚህ በፊት የተለመደው የፈውስና የብልጽግና መንገድ አልሠራ ሲል አሁን የተጀመረው ደግሞ ከፈውሱ ይልቅ የበሽታውን፥ የድኅነቱን፥ የስኬት ጎዶሎነቱን ምንጭ አነፍንፎ በመፈለግ ያንን መስበር ነው። ይህ የጉድለት ምንጭ ወይም እርግማን የሚታወቀውም እነሱ 'የመገለጥ እውቀት' በሚሉት የማወቂያ መንገድ ነው። ይህ ተደርጎም ያ ሰው ካልተፈወሰ ወይም ካልበለጸገ ቀድሞ እምነት ጎድሎት ነው እንደሚሉት አሁንም እርግማኑን ስላልሰበርክ ነው ብለው ኃላፊነቱን በሰውየው ትከሻ ላይ በመጣል እነሱ እንደቀድሞው ሁሉ ንጽሕናቸውን ይዘው ይቀመጣሉ።

ማሪሊን በመጽሐፏ ከጠቀሰቻቸው እርግማኖች መካከል አንድ ቤተ ሰብ እርሻው ፍሬያማ ያልሆነው የተደባለቁ ከብቶች ስለሚያረቡ በመሆኑና ይህ ደግሞ በዘጸ. 19፥19 የተከለከለ በመሆኑ ነው።[35] ይህ ብቻ አይደለም፤ በሰው አካል፥ በቤተ ሰቡ፥ በመንፈሳዊ፥ በማኅበራዊ፥ በልቡናዊ ሕይወቱ የሚደርሱ እንደ ራስ ምታት፥ የልብ በሽታ፥ የልብ ድካም፥ የነርቭ በሽታ፥ እንቅልፍ ማጣት፥ የአጥንት በሽታ፥ የዝቅተኝነት ስሜት፥ ዓመፀኛ ልጆች፥ ያልዳኑ የቤተ ሰብ አባላት፥ ድህነት፥ መነጽር ማድረግ፥ ወዘተ ሁሉ እርግማንና የእርግማን ውጤቶች ናቸው።[36] ስለመነጽር እንዲህ ብላለች፥ "እያንዳንዳቸው መነጽር የሚያደርጉ አንዳንድ ቤተሰቦችን አይታችኋል? አባት፥ እናት፥ ትንሽ ልጅ ሳይቀር መነጽር ያደርጋሉ፤ ያውም ባለወፍራም ሌንስ መነጽር። እነዚህ ምስኪን

35 Hicky, p. 7.
36 Ibid., pp. 137-155.

ሰዎች በእርግማን ስር ነው ያሉት፤ ከዚህ ነጻ መውጣት አለባቸው።”[37] መጽሐፉ እንደ ንስሃና ይቅርታ የመሰሉ አንዳንድ መንፈሳዊ ቁም ነገሮችን የያዘ ቢሆንም በማዕከላዊ ትምህርቱ የተቃወሰ ስነ መለኮት የተነሣ ከሚለቀሙት መልካም ነገሮች ይልቅ አሳሳቾቹ ትምህርቶች ይበዛሉ። ጸሐፊዋ ይህ እርግማን ብዙውን ጊዜ የተወረሰ እርግማን መሆኑን፥ አንዳንዴ ደግሞ ከሌላ ሰው የተወረወረ እንደሚሆን ትናገራለች። ዘዳ. 29፥21-25ን በመጥቀስም ማናቸውም በሽታ በኃጢአት ወይም በቀደሙ ወላጆች እርግማን የመጣ ነው ትላለች። በዮሐ. 9 እንደተጻፈው የጌታ ደቀ መዛሙርትም እንደ አይሁድ ትምህርት ሁሉ ይህን ያምኑ ነበር። ጌታ ግን ይህን አመለካከታቸውን ደግፎ አልተናገረም። ማሪሊን ስለ መገለጥ እውቀት አስመልክታ ስትናገር ሆሴ. 4፥6ን፥ “ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል” የሚለውን ጠቅሳ ጽፋለች።[38] ይህን የጠቀሰችው በተውልድ የሚጠላለፍ የዐይን ሕመም ያለባቸውን ቤተሰብ አውስታ ያ ቤተ ሰብ እርግማናቸውን ባለማወቃቸው እየጠፉ መሆናቸውን ነበር። በዚህ ክፍል ቃሉ የሚለው እውቀት ማጣት ምንነት ግን በቁጥር 1 ላይ ተጽፎ ይገኛል። አረማዊ ትምህርቶች በጥቅስ እየተጠቀለሉ ለጉርሻ ሲቀርቡ ማለት እንዲህ ነው። ማሪሊን በመጽሐፍዋ ከጠቀሰቻቸው መርገሞች ዓይነትና ብዛት ከተነሣን እያንዳንዱ ክርስቲያን የተረገመ ነው ብሎ ለመደምደም ያስደፍራል። በ60ዎቹ በአገራችን ክርስቲያኖችን ሁሉ አጋንንት አለባቸው እያሉ ከሚያስተምሩት ጋር በዓይነቱ የሚቀራረብ ትምህርት ነው።

ብዙ የስሕተት ትምህርቶች የሚነሡት በጣም ግልጽ ካልሆኑ ክፍሎች ነው። እንደሌሎች ጥቅሶች ግልጽ ያልሆኑትን በመውሰድ የስሕተት ትምህርቶቻቸውን ይደግፉበታል። ሐተታቸውም ሆነ የችግሩ መንስዔና መፍትሔ የሚመነጨውም ከቃሉ ውስጥ ሳይሆን ከቃሉ ውጭ ከሆነ የመገለጥ እውቀታቸው ነው። ክርስቲያኖችም የክፍሉን ምንነት በሚገባ ካላወቁት እንዲያ ማለት ሳይሆን አይቀርም ብለው ስለሚቀበሉት ትምህርቱን ከነስሕተቱ ይቀበሉታል። የዘር ማንዘር እርግማን ትምህርትም ከዚህ ያልተለየ ነው። ቃሉን የሚያጠኑ ክርስቲያኖች እንዲህ የመሰሉ ትምህርቶችን ሲጋፈጡ ግልጽ ካልሆኑ ጥቅሶች ከተንደረደረው ትምህርታቸው ቀጥሎ በዚያ ርዕስ ላይ ግልጽ በሆነ ሁኔታ በቃሉ ውስጥየተጻፈ ትምህርት መኖሩን መመርመር አለባቸው።

ይህንን ትምህርት የሚያስተምሩት የማሪሊንም ሆነ የሌሎች ካሪዝማውያን አስተማሪዎች የእርግማን ትምህርት የተቃወሰ

[37] Ibid., p. 46.
[38] Ibid., pp. 78-79.





ስነመለኮትነቱ በመጀመሪያ ደረጃ ከክርስትና እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይልቅ በዓለም ፍልስፍናና በአጋንንታዊ አምልኮ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች እንደሚኖሩበት ባለ ፍርሃት ውስጥ ክርስቲያኖችንም ማኖሩ ነው። አዲስ ፍጥረት የሆነው ሰው እርሱ ያላደረገውና ያላወቀው የሌላ ሰው ጥፋትና ኃጢአት ሰለባ ሊሆን ነው። ይህንን እርግማን ተቆናጥጦም ሰይጣን ክርስቲያኖችን ሊያማስል ነው ማለት ነው። ክርስቲያኖችንም ጨምሮ ሰዎች ሁሉም ‘በመገለጥ እውቀት’ ይህ እርግማን ምን መሆኑን አውቀው እርግማኑንም ሰይጣንንም በቃል ተናግረው ነጻ መውጣት አለባቸው። የመገለጥ እውቀት የሚባለው እስኪመጣላቸው ታስረው ይቆያሉ። ሲመጣላቸውም የሚናገሩት ላመኑትና ለታመኑበት ጌታ ሳይሆን ለሰይጣን ነው። በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን የምናገኘው እምነት ግን ሰው እምነቱን በእግዚአብሔር አምላክ ላይ ሲያደርግ በእርሱ ጥበቃና መልካምነት ስር እንደሚሆን ነው። እንደ ማሪሊን ድምዳሜ እርግማኖች በክርስቲያኖች ላይ የሚመጡበት መንገድ ልክ ኒል አንደርሰን እንደደረሰበት ያለ ነው። አንድ ችግር በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ከመጣ የቀደሙት ወላጆቹ ወይም ሌላ ሰው ረግሞት ለሰይጣን ችግር እንዲያመጣበት መብት ሰጥቶት ነው ማለት ነው ይላሉ። ወይም ኢዮብን በመጥቀስ ራሱ በራሱ ላይ ተናግሮ ሰይጣን ያመጣበት ፍዳ ነው ይላሉ። እርግማኖች እንደ ወፍ በዙሪያችን እየበረሩ ያሉ ያስመስሉታል። አንድ ወይም ብዙ እርግማን ከዚህ በፊት የወደቀበት ክርስቲያን ከዚህ በኋላ እንደማይደርስበት ዋስትናው ምንድርነው? አንዳንድ አስተማሪዎች የመርገም መስበሪያውን ቃል ደጋግመው እንዲሉት ያስተምራሉ። ልክ እንደድግምት ማለት ነው። ይህ አልሠራ ካለ ጥፋት ከትበው በአንገት ላይ ሳያስነግቱ የሚቀሩ አይመስልም።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳን ከተጋባቸው ሰዎች ወይም ሕዝብ ጋር ያደረገው ስምምነት እነዚያ ሰዎች ያንን ቃል ኪዳን ቢጠብቁ በብዙ መንገድ እንደሚባርካቸው ቢያፈርሱ ደግሞ መርገም እንደሚሆንባቸው፥ ማለትም፥ በረከቱ እንደሚቀርባቸው ብቻ ሳይሆን ቅጣት እንደሚመጣባቸውም ነው። ይህ ደግሞ በቃል ኪዳኑ ውስጥ የተዋዋሉት ስምምነት እንጂ ሰይጣን የሚያወርድባቸው መቅሰፍትም አይደለም። ይህ የሚሆንባቸው በዓላማ ነው። ዓላማውም ወደ አምላካቸውና ወደ በረከቱ እንዲመለሱ ነው። በዘጸ. 20፥3-5፤ ዘዳ. 5፥8-10፤ 7፥9-10፤ ወዘተ፥ ያሉት ጥቅሶች በመጀመሪያ ደረጃ ስለእግዚአብሔር ማንነት የሚያውጁ ቃላት ናቸው። ማንነቱም መልካምነቱና ቀጪነቱ ና ቸው። እግዚአብሔር መልካምና ቸር አምላክ የመሆኑን ያህል የሚቆጣና የሚቀጣ ጌታም ነው። እርሱ ጻድቅ ፈራጅ ነው። የእግዚአብሔር ባህርይ አሁንም እንደ ጥንቱ ነው፤ አልተለወጠም። አሁንም ቸርም የሚቀጣም አምላክ ነው። ከዚህ የእግዚአብሔር ቸርና ጻድቅ ቀጪነት ባህርይ ሌላ ቀጪው እራሱ እግዚአብሔር እንጂ ያለቦታው የሚገባ ሰይጣን አለመሆኑን ማወቅ አለብን።

ደግሞም የሁለቱን ኪዳኖች ልዩነት ማስተዋል አለብን። በአዲሱ ኪዳን በክርስቶስ ያመንን ክርስቲያኖች በአሮጌው ሕግ ስር አይደለንም። በመስቀሉና በደሙ የተፈጸመው ኪዳን አዲስ ቃል ኪዳን ነው። ይህ ነው አዲስ ኪዳን የተባለው። ይህ በስነ ትርጓሜ ክፍል ውስጥ ሐተታ ተሰጥቶበታል። ክርስቶስ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ እኛን ከሕግ እርግማን፥ ማለትም ከሕግ ኮናኝነትና ከሳሽነት ዋጅቶናል፤ ገላ. 3፥10-14።

ይህ ማለት ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ መርገም ወይም እርግማን የሚባሉ ቃላት የሉም ማለት አይደለም። አሉ። ሰዎች ሰዎችን ይረግማሉ፤ የጌታን ተከታዮችም ሊረግሙ ይችላሉ፤ ማቴ. 6፥44-45፤ ሉቃ. 6፥28፤ ይህ ከሆነ ቃል ተናግረን ያን መርገም እንድንሰብር ሳይሆን ጌታ ያስተማረን የሚረግሙንን እንድንመርቅ ነው። እንዳንረግምም ቃሉ ያስተምራል፤ ሮሜ. 12፥14፤ ያዕ. 3፥9። ጳውሎስም በተለያየ መልኩ ቃሉን ተጠቅሞበታል፤ ሮሜ. 9፥3፤ 1ቆሮ. 16፥22፤ ገላ. 1፥9። ግን ሰይጣን የዘመዶቻችንን የሌሎችንም እርግማን በእኛ ላይ አምጥቶ እንደሚቆልል፤ ይህ መርገም መኖር አለመኖሩ በመገለጥ እውቀት ብቻ እንደሚታወቅ፤ ከዚህ የመውጫው መንገድ የመገለጥ እውቀቱ አለን የሚሉ ሰዎች የሚሰጡንን የቃል ቀመር በመድገም መስበር መሆኑን ቃሉ አያስተምረንም። በአዲስ ኪዳን ይቅርና በአሮጌው ኪዳንም ቢሆን ቃል ኪዳኑን ቢያፈርሱ ቅጣቱ ከእግዚአብሔር ይመጣባቸው ነበር እንጂ የሌላው እርግማን እንደማይደርስባቸው የበለዓም ታሪክ ያስተምረናል፤ ዘኁ. 22-24። የበለዓም ምዋርትና እርግማን በእስራኤል ላይ ከቶም አልደረሰም። እንዲያውም በ23፥23 ላይ እንደምናገኘው፥ "በያዕቆብ ላይ አስማት የለም፤ በእስራኤልም ላይ ምዋርት የለም" ብሎ ራሱ ተናገረ። በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ምዋርት የለም።

በሕዝቅኤል ዘመን የነበሩ አይሁድ በእነርሱ ላይ የደረሰው መከራና ጉስቁልና፥ ምርኮና ግዞት እነርሱ ባደረጉት ጥፋት ሳይሆን አባቶቻቸው በሠሩት ክፋት ያገኛቸው መሆኑን ለመጥቀስ፥ "አባቶች ጨርቋ የወይን ፍሬ በሉ፤ የልጆችም ጥርሶች ጠረሱ" ብለው ምሳሌ ይመስሉ ነበር፤ ሕዝ. 18፥2። ይህ እራስን በራስ የማጽደቅ ጥረት ነው። በዚህ ክፍል ነው ጌታ በነቢዩ አማካይነት ይህ ምሳሌአቸው ትክክል ያለመሆኑን ብቻ ሳይሆን ኃጢአት የግል፥ የነፍስ ወከፍ መሆኑን በሰፊው ያስተማረው። ምርኮውን እግዚአብሔር ለቅጣትና በራሱ ጊዜ ነው ያመጣባቸው። የቀደመው ታሪካቸው ሲመረመርም ይህ ከእግዚአብሔር ብዙ ትእግሥት በኋላ የመጣ ቅጣትና ከጣዖት አምላኪነታቸው ለመለየት ፈቅዶ ያመጣባቸው የቃል ኪዳኑ አንድ ክፍል ነው። በብሉይ ኪዳን የበረከት ምንጭ በኪዳኑ ውስጥ በታማኝነት መኖር ነው። መርገም





የሚመጣባቸው በኪዳኑ ውስጥ በግልጽ እንደተነደፈው ከኪዳኑ ውስጥ ሲወጡ ነው።

በአዲስ ኪዳንም አማኞች በክርስቶስ ኢየሱስ በረከት ተባርከዋል። በእርሱ ውስጥ በመኖርና እርሱን በመታዘዝ መጽና ታቸው በበረከቱ ውስጥ መኖራቸው ነው። በረከት ሲባል ግን ሁሌም ቁሳዊና አካላዊ ብቻ አለመሆኑም ሊጤን ይገባዋል። በክርስቲያኖች ላይ ሊደርስ ስለሚችል እርግማን በገላትያ መልእክት ውስጥ እናገኛለን። ይህ እርግማን ግን የዘር ማንዘር እርግማን ከቶም አይደለም። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደምናገኘው አሕዛብ በእምነት በክርስቶስ በኩል በተፈጸመው ሥራ የአብርሃምም በረከት ተቀባዮች እንደሆኑ ተጽፎአል፤ 3፥8-9። ቀጥሎ ባለው ክፍል እንደምናገኘው የተረገሙት ከሕግ ሥራ የሆኑቱ ናቸው፤ 3፥10-11። ከሕግ ሥራ ሲባልም ሕግን በመፈጸም ለመጽደቅ የሚጥሩት ና ቸው፤ ምክንያቱም በተጻፈው ሕግ የማይኖርና የማያደርግ የተረገመ እንደሆነ ተጽፎአልና። ሕግን ፈጽሞ የጠበቀና የዳነ ሰውም የለም። ይህ ስለሆነም ነው ክርስቶስ ሥጋን ለብሶ የመጣውና ያዳነን። የገላትያ ምዕመናን በጸጋ ከዳኑ በኋላ በሕግ ሥራ ለመጽደቅ ሊታገሉ ወደ አይሁድ ሥርዓትና ወደ አባቶች ወግ፥ በተለይም ወደ መገረዝ ሥርዓት፥ የሚመራ ልዩ ወንጌል ሰምተው ዘወር ማለት ጀምረዋል። መጽደቅ በሌላ በምንም ሳይሆን በእምነት ብቻ መሆኑን በማሳየት ነው ጳውሎስ በዚያ ሥርዓት ስር መሆንን እርግማን ነው የሚለው። ከዚህ ጠብቀው ሊድኑበት ከማይቻለው ሕግ እርግማን ክርስቶስ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ ነው ያዳነን፤ 3፥13-14። የእርግማን መንስዔ ኃጢአት ሲሆን ክርስቶስ ላመኑት እርግማን ሆኖ ነው ከዚህ እርግማን የዋጃቸው።

እንግዲህ የትውልድ እርግማንን በክርስቲያኖች ጫንቃ ላይ የሚጭኑት አስተማሪዎች ስሕተት ግልጽ ነው። አንድ ክርስቲያን ካመነ በኋላም በእርግማን ሥር መሆኑ በነዚህ አስተማሪዎች ተደጋግሞ ይነገራል። ይህ አንዳንድ ፈውሰኞች የመገለጥ እውቀትን አሳብበው በመላ ምት እንደሚሠሩት ካለው ልምምድ ያልተለየ ነው። ልዩነቱ ፈውሱ ካልታየ በሽተኛው እምነት ጎድሎት መሆኑ ሲነገር በዚህኛው ደግሞ በበሽታው ወይም በድህነቱ መጥፋት ላይ ሳይሆን ረቂቅ በሆነ መንገድ ወደ ምንጩ መሄዳቸውን መምሰሉ ነው። ውጤት ካልታየ አሁንም ችግሩ በችግረኛው ላይ ተለጥፎ የሚቆይ ነው የሚደረገው። ዴረክ ፕሪንስ የተባለ ሌላው የዚህ ትምህርት ሰባኪም ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ዘጸ. 20 በመጥቀስ እርግማንን ጣዖት ሲያመልኩ ከኖሩ የቀደሙ ወላጆቻችን የወረስነው በሕይወት ውስጥ የተተከለ ወደ ስርና ወደጎን ከሚያድግ አረም ጋር ያመሳስለዋል። ይህ አረም እስካልተነቀለ ድረስም አንድ

ክርስቲያን የክርስቶስን ሕይወት ሙላት መለማመድ አይችልም።[39] ከአበሻ ሰባኪዎችም በናሙና ኮንፈረንስ ንዑስ ምዕራፍ ስር የተጠቀሰው ሰባኪ፤ *"አንዳንዱ ደግሞ በጣም ሰነፍና ፋሊሽ የሆነ ክርስቲያን ምን ይላል፥ እኔ ክርስቲያን ነኝ በክርስቶስ መርገም የለብኝም ይላል። በክርስቶስ ካለህ ለምን በመርገም ትኖራለህ ታዲያ? ለምን በድህነት ትኖራለህ? ለምን በበሽታ ትኖራለህ? ለምን ያለመከናወን አለብህ? ስላመንክና ዳግም ስለተወለድክ መርገሙ አይሄድም* ያለውን ልብ እንበል። ዴረክ በኛ ላይ በቀጥታ መርገም የሚያመጡብንን ሰዎች ወደ አራት ትውልድ በመውጣት 30 ያደርጋቸዋል፤ ሁለት ወላጆች፥ አራት አያቶች፥ ስምንት ቅድመ አያቶችና አሥራ ስድስት ቅም ቅም አያቶች። ክርስቲያኖችንም ጨምሮ አሁን ባለው ትውልድ ላይ አሁን የሚመጣው ማናቸውም ችግር ወይም እርግማን ከነዚህ አንዳቸው ከሠሩት በደል የተነሣ የሚመጣ ነው ብሎ ይደመድማል።[40] አማኙ ካመነና ከዳነ በኋላም የነዚህ ሰዎች የመገለጥ እውቀት እስኪገለጥ ድረስ ዘመኑን ሁሉ በፍርሃት ሊኖር ነው ማለት ነው። ደኅንነቱንም ሙሉ ለማድረግ የዚህ እውቀት መገለጥ ካስፈለገ የክርስቶስ የማዳን ሥራ ሙሉ ላይሆን ነው። በክርስቶስ የማዳን ጸጋ ላይ ሌላ የመገለጥ እውቀት ያስፈልጋል የሚል ማሚያ ነው ስህተቱ። በአንድ በኩል የክርስቶስን ሥራ ማጉደል፤ በሌላ በኩል ደግሞ የደኅንነት ማሚያ መጨመር ነው።

## *የኤድስ 'ፈውስ'*

*በመንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች* መጽሐፍ ላይ በተጠቀሰው በመቱ የተደረገ የፈውስ ጉባኤ ላይ ልትፈወስ ሄዳና 'ተፈወሰች' ተብላ እመድረክ ላይ ስለሞተችውና ሬሳዋ ስለወጣው ሴት ተወስቶአል። በዚያው ሴቲቱ የሞተችበት ጉባኤ ላይ የተነገረ ሌላ ፈውስም ነበረ። የኤድስ ፈውስ። በዚያ የነበረ አንድ ወጣት የኤድስ በሽታ እንዳለበትና እንደተፈወሰ ያው በዚያ የተጠቀሰ ፈውሰኛ ተናገረ። የከተማዋ ሕዝብ እስኪሰሙት ድረስ ይህ የፈውስ ዜና ተስተጋባ። እኅቱም፥ 'የሰው አፍ የገባው ወንድሜን ጌታ ኅበኘው' እያለች ብዙ የምስጋና ምስክርነት ቃል ተናገረች። በማግስቱ በነበረው ቀጣይ የፈውስ ጉባኤ ላይ የተፈወሰው ወጣት እንዲመሰክር ጊዜ ተይዞለት ነበር። ቢጠበቅ የለም፤ ሲፈለግም በአምቡላንስ ወደ ሆስፒታል መወሰዱ ተሰማ። ከጥቂት ቀናት በኋላ

[39] Prince, p. 64.
[40] Ibid. 74.





ከሆስፒታል ወጣ። ድኖ ሳይሆን በዚያው ሕመም ሞቶ ነበር የወጣው። ሌሎችም ጥቂት ያልሆኑ በኤድስ የተያዙ የነበሩና እንደተፈወሱ በግልም በአደባባይም እየተነገረ ግን የሞቱ ሰዎችን አውቃለሁ።

እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ ነውና ሰዎችን ከምንም ዓይነት በሽታና መቅሰፍት ሊያድን እንደሚችል ፈጽሞ መጠርጠር የለብንም። እግዚአብሔር ሊፈውስ ይቻለዋል፤ ግን የውሸት ፈውሶችን እንደ እውነት መቀበል በክርስቶስ ከማመናችን ጋር አብሮ የተሰጠን ግዴታ አይደለም። ከኤድስ የተፈወሱ ሰዎችን እንደተፈወሱ ከመቀበል ብቻ ባሻገር ማረጋገጥ አስፈላጊና እንደ ዘበት ሊታለፍ የማይገባው እውነት ነው። ከኤድስ እንደተፈወሰች ከተነገራት አዘውትሬ ከምሄድባት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካለች አንዲት ልጅ የፈውስ ማረጋገጫ ለማግኘት ሞክሬ ነበር። ያገኘሁት መልስ ግን ይህንን ማረጋገጫ ለማግኘት አሳቡን ራሱን ማስተናገድ ተመልሶ በበሽታው ጭንቀት ራስን እንደማጠላለፍ ብቻ ሳይሆን እንደ አለማመንም እንደሚቆጠር ነበር። መጠየቁም እምነትን እንደመንደል እንደሚያስቆጥርም ነው የተነገረኝ።

*ተአምራት* በሚል ርእስ በፓስተር ሰይፉ ከበደ የተጻፈ መጽሐፍ ውስጥ ጸሐፊው ካያቸው ተአምራት ዝርዝር ውስጥ የኤድስ መመታትም ይገኝበታል። የእግዚአብሔርን ፈዋሽነት ባልጠራጠርም የሰማኋቸውና የገጠሙኝ የኤድስ ፈውሶች ሁሉ ውሸት ሆነው ስላገኘሁ ተጨባጭ መልስ ለማግኘትና ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ከኤድስ የተፈወሱ ሰዎችን ስምና አድራሻ ከደራሲው ጠይቄ ነበር። እስከዚህ ጽሑፍ ሕትመት ድረስ መልስ አላገኘሁም።

በናሙና ኮንፈረንስ ምዕራፍ የተጠቀሰው ሰባኪ አሁን ከምኖርበት ስፍራ ባልራቁ ሁለት የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ከኤድስ የተፈወሱ ሰዎች መኖራቸውን በዚያው ጉባኤ ላይ ሰብኮ ነበር። ይህን ለማረጋገጥ ከመጋቢዎቹ ማረጋገጫ ላገኝ ሞከርኩ። እነዚህ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ያሉአቸው ምዕመናን ጥቂት ስለሆኑ እንዲህ ያለ ነገር ቢከሰት በመጋቢዎቹና በምዕመናኑ ቀርቶ እውጭ ባሉትም በብዙዎች ይታወቃል። ግን ከኤድስ እንደተፈወሱ ማረጋገጫ የሚያስጨብጡ በሽተኞች በሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት አልነበሩም። ለምሳሌ፥ ከሁለቱ የአንደኛዋ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንዲያ ያለ ሰው መኖሩን ስጠይቀው "አዎን" አለኝ። እርግጠኛ ፈውስም እንደሆነ ነገረኝ። ያ ሰው ስለመፈወሱ በሐኪም የተረጋገጠ ወረቀት እንዳለው ጠየቅኩት። እንደሌለው ነገረኝ። ቀድሞ የኤድስ በሽተኛ ለመሆኑስ ማረጋገጫ እንዳለው ስጠይቅ አሁንም እንደሌለው ነገረኝ። እንግዲህ ይህ ሰው በኤድስ የተያዘም ሆነ የተፈወሰ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የለም። ይህንን ነገር ለማረጋገጥና እውነትነቱን ለማጣራት እንደምፈልግ ነግሬ ከሰውየው ጋር ለመገናኘት እንዲረዳኝ ጠየቅኩት። ለዚህ ጥያቄ የተሰጠኝ መልስ ጠንካራ

“አይቻልም” ነበር። ለምን እንደማልችል የነገረኝም የይሉኝታ ችግር፥ የባህላችን ምስጢር የመደበቅ ነገር፥ እንዲሁም ሰውየው በኤድስ መያዙን ሰዎች ካወቁበት ምን ይሉኛል ባይነቱ ነበር። መጋቢው ግን ፈውሱን ያምናል። እንዴት እንዳመነ ስጠይቀው በሽተኛው በግል ካጫወተው በመነሣት ሲመረመር የኤች አይ ቪ ካውንቱ ወይም በደም ሴሎች ውስጥ የሚቆጠረው የቫይረስ መጠን እንደቀነሰ በመናገሩ ነው። ይህ ‘ካውንት’ የሚባለው ደም ወስደው ሲመረምሩ በደም ውስጥ ያለው የቫይረሶቹ ቁጥር ሲጨምርና ሲቀንስ የሚሆነው ነገር ነው። ይህ ቁጥር አንዳንዴ ይጨምራል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ይቀንሳል። እንግዲህ ያ ሰው ተፈወሰ ከተባለ በኋላ በአንዱ ምርመራ ወቅት የቫይረሱ ካውንት ቀነሰ እንጂ እንዳልተፈወሰ ግልጽ ነው። ይህ ሰው ቀድሞም ኤድስ እንዳለበት ሳይታወቅ፥ ኋላም ተፈወሰ ተብሎ በጉባኤው ውስጥ ይገኛል።

እግዚአብሔር ፈዋሽ ነውና ቢፈውስ መደነቅ አለበት። የዚያኑ ያህል ደግሞ ያልተፈወሱትን እንደተፈወሱ የሚናገሩ ፈውሰኞች ስሕተታቸው ሊነገራቸው ይገባል። ችግሩ የፈውስ ስጦታ አለን ባዮቹ ብቻ አይደለም። ከበሽተኞችም ሳይፈወሱ የተፈወሱ እየመሰላቸው የተሞኙ ጥቂት አይደሉም። አንዳንዶች በየዋኅነት ከኤድስ መፈወሳችሁን ተቀበሉ ስለተባሉ ጉም እየዘገኑ ሳይመረመሩ የትዳር ጓደኛ ፈልገው እያገቡ ለሌላ ጠንቅ የሆኑ አሉ። አንዳንዶቹ ከልባቸው ያለመፈወሳቸውን እያወቁ ግን እንደተፈወሱ ሆነው ቀድሞ ያጡትን ተቀባይነት አግኝተው እየተደሰቱበት መጠቀሚያ ያደረጉትም አሉ። እንዲህ ያለ አንድ ደፋር ሰው አይቻለሁ። ደፋር ያልኩት በየዋኅነት ተፈውሻለሁ ብሎ የሚወዛወዝ ሳይሆን ሊያጭበረብርበት የሚሞክር መሆኑን በማረጋገጥም ነው።

የዚህ ሰው ‘ፈውስ’ ታሪክ እንዲህ ነው። በ89 ዓመተ ምሕረት ታኅሣስ 13 ቀን በአዲስ አበባ ባለች አንዲት የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ጊዜ አንድ ሰው ከኤድስ እንደተፈወሰ መሰከረ። እንዲፈወስ የጸለየለት ሰው በዕለቱ ይሰብክ ነበርና ከስብከቱ ጊዜ ቀርቶ ለተፈወሰው ሰው በሰጠው የምስክርነት ዕድል ነው ምስክርነቱ የተደመጠው። ሰውየው እንዴት በመሰለ አስደናቂ ሁኔታ ጌታ እንደፈወሰው መሰከረ። ጉባኤውም በተለመደ የተጋነነ ሆታና እልልታ ቤቱንም ዳሱንም ሞላው። በጊዜው በቃለ ሕይወት ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት ውስጥ እሠራ ነበርና የፈውሱን ዜና ሰማሁ። ይህ ከሆነበት ቀጥሎ ባለው ሳምንት አጋማሽ ላይ ከሥራ ባልደረባዬ ጋር በመሆን በዚያችው በተፈወሰበት ቤተ ክርስቲያን ለዚሁ ሰው ቀጠሮ ተይዞ ቃለ መጠይቅ አደረግንለት። ከሕመሙ እንዲፈወስ የጸለየለትንም ሰው አነጋገረን ነበር። ሁለቱንም ያነጋገርነው እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ ነውና ይህ ነገር እውነት ከሆነ የእግዚአብሔር የፈውስ ሥራ አዋጅ ተብሎ እንዲነገር፤ ካልሆነም ውሸታም ፈውስ ነውና ከሐሰተኛ ፈውሰኞችና ተፈዋሾች ሰዎች እንዲጠነቀቁ ምዕመናንን ለማሳሰብ ነበር።





እንደተፈዋሹ ምስክርነት በጦር ሠራዊት ውስጥ ሲያገለግል ሳለ በበሽታው እንደተለከፈና በተጨማሪም የሳንባ በሽተኛ መሆኑንም ነገረን። የሳንባ በሽተኛ ለመሆኑ ከሳንባ ነቀርሳ ክሊኒክ የተሰጠውን መታወቂያ ለማረጋገጫ አሳይቶናል ከዚህኛው ሕመም መፈወሱን ግን አልተናገረም። በዚያው መታወቂያ ላይ የተጻፈው በሐኪም እንደሆነ የነገረን የኤድስ በሽተኛ መሆኑን የሚመሰክር የእጅ ጽሑፍም አለበት። ሰውየው ስለ ሕመሙ በሰፊው ከነገረን በኋላ ስለ ፈውሱም በሰፊው መሰከረልን። ከሦስት ሳምንታት በፊት በቤተ ክርስቲያኒቱ በሚደረገው መደበኛ የዐርብ የጸሎት ጊዜ ተገኝቶ ሳለ አገልጋዩ እጁን ጭኖ ሲጸልይለት ኃይለኛ እንደ ኮረንቲ ያለ ንዝረት እንደተሰማውና በሰውነቱ ላይ የነበረው ቁስል በማግስቱ እንደደረቀ ነገረን። ወደ ሐኪሞቹም ዘንድ ሄዶ መፈወሱን እንደነገራቸውና እነርሱም እንደገና መርምረው ነጻ መሆኑን እየተገረሙ እንደነገሩት አወጋን። አስፈላጊ ማስታወሻዎችንና ምስሎችን ከወሰድን በኋላ ለሚቀጥለው ቃለ መጠይቅ ከሐኪሞቹ የተሰጠውን ከኤድስ ነጻ የመሆኑን ማረጋገጫ ወረቀት እንዲያመጣና እንዲያሳየን፥ የሐኪሞቹንም ስምና አድራሻ እንዲሰጠን ተስማምተን ቀጠሮ ይዘን ተለያየን።

በቀጣዩ ቀጠሮ በተባለው ሰዓት ቃለ መጠይቁን ያደረግነው ሁለታችን እንዲሁም የክፍላችን አለቃና የመሥሪያ ቤታችን የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ሠራተኛ ተያይዘን ሄድን። በቀጠሮው ጊዜና በቦታው ተገኝተን ሁለት ሰዓት ያህል ከጠበቅነው በኋላ ስላልመጣ ትተን ተመለስን። በቃለ መጠይቁ ወቅት የያዝናቸው ውሸት እንደሆኑ የተረዳናቸው ነጥቦች ነበሩ። በዚያው ቀን ስለ እርሱ ሌላ አስደንጋጭ ነገር ሰማንና ያንንም ለማስረገጥ በሳምንቱ ውስጥ አስፈልገን ልናገኘው አልተሳካልንም። የዚህኛውን እውነትነት ለማረጋገጥ ግን ከሚያውቁት ሦስት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጋር ባደረግነው ቃለ መጠይቅ ይህ ሰው ከዚያ ጊዜ ሁለት ዓመታት በፊት በቀጠና ሁለት ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ከኤድስ ተፈወሰ የተባለለትና እርሱም ተፈወስኩ ብሎ ሰፊ አድናቆትን ያተረፈ፥ በአንድ ክርስቲያናዊ ጋዜጣም ታሪኩ የተጻፈለትና ብዙ የዋህ ክርስቲያኖችም በተለያዩ መንገዶች የገንዘብና ሌሎችም እርዳታ ሲያደርጉለት የቆየ ሰው መሆኑን፥ አሁን ያ እርዳታ ከወዲያ በኩል ሲመነምን ወደዚህችኛዋ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ተመሳሳይ ድራማ ሊሠራ እየሞከረ መሆኑን ነገሩን። ደፋሩን ሰው ከዚያ በኋላ ልናገኘው አልቻልንም። እንደፈወሰው ለመሰለው ሰው ግን ጉዳዩን ስንገልጥለት አገልጋዩ የእርሱን ጸጋ እንዳጣጣልንበት ብቻ ነበር ጉዳዩን የወሰደው እንጂ የአደጋው ግዝፈት አልታየውም። የውሸት ፈውሶችን ያለፈቃድ እያባዙ የሚሸጡ ፈውሰኞች ዝም መባል ያለባቸው እስከ መቼ ነው? ፈውሶችስ በማይረጋገጡ በሽታዎች ብቻ ላይ ተጣብቀው የሚቀሩት እስከመቼ ይሆን?

የውሸት ፈውሶች በፈዋሾችም ይደረጉ ወይም በተፈዋሾች ችግራቸው ቶሎ የሚቀረፍ አይደለም። ከፈውሱ ያለመኖር አካላዊ ጉስቁልና ባሻገር ስሜታዊና መንፈሳዊ ኪሳራ አለበት፤ በማያምኑትም ዘንድ ሳይቀር የሚፈጠር የስም መጉደፍና ሞራላዊ ዝቅታ ይከተላል። ይህ ደግሞ በተራው የወንጌል ሩጫን የሚያስዘግምና ምስክርነትን የሚያጎድፍ ነው። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በኬንያ ውስጥ እንዲህ ያሉ የውሸት ፈውሶች እጅግ እየበዙ ውሸትነታቸው በአማኞችም በዓለማውያንም ዘንድ በግልጽ እየታየ መጥቶ የቤተ ክርስቲያን መነወሪያና የእግዚአብሔር ስም መሰደቢያ ሆኖ ነበር። *The Nation* የተባለ የአገሪቱ ጋዜጣ ስለነዚህ የተአምር ፈውሰኞች *እነሆን የተአምር ነጋዴዎች አስወግዱልን* በሚል ርእስ አንድ መጣጥፍ ጽፎ ነበር። በውስጡ ከተጻፈው መሐል፣

> እነዚህ ዳንን የሚሉ ሰዎች እነማን ናቸው? ከየት ነው የመጡት? ለምንድነው ሁሌ እንግዳና የማይታወቁ የሚሆኑትና ከዚያ በፊት ያልታወቁ ከዚያም በኋላ የማይገኙ የሚሆኑት? እንደሚታወቀው እያንዳንዲቱ የኬንያ ከተማ የሚታወቁ ዐይነ ስውር ለማኞችና አካለ ስንኩላን አሉአት። ከእነዚህ አንዳቸው ተፈውሰው ቢሆን የከተማዋ ነዋሪዎች ሁሉ ተአምር መፈጸሙን ያምኑ ነበር። ይሁን እንጂ እኒህ ታላላቅ ወንጌላውያን መጥተው ሲሄዱ ዕውርና አንካሳ ለማኞቻችንን እዚያው የነበሩበት ነው የምናገኛቸው። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ተአምራዊ ፈውስ ልማድ ከቶም አይደለም። እነዚህ ወንጌላውያን በስሙ የሚነግዱበት ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራቱን ይፈጽም የነበረው በስውር አልነበረም፤ ደግሞም ሰዎች እውነትነቱን እንዲያረጋግጡት አይከለክልም ነበር። በሉቃ. 5፥12 ኢየሱስ ለምጻሙን ከፈወሰ በኋላ ሰውየው ወዲያው ሄዶ ራሱን ለካህናት እንዲያሳይና መፈወሱ እንዲረጋገጥ ነበር የላከው።[41]

ይህ ከአማኙም ከአላማኒውም ሰፊ ተነባቢ ያለው ብሔራዊ ጋዜጣ ነው። ፈውሶቹ ሐሰተኞች ከሆኑ የሚስተጋባው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። ወደ ኤድስ ስንመለስ ደግሞ ቀሳፊነቱና ተዛማችነቱ የፈውሱን እርግጠኛነት የሚያስጠይቅ ቢሆን ይህን ማረጋገጫ መጠየቅ የሌሎችን እምነትና ፈውስ እንደማፍረስ፣ እንዲሁም እንደ ነውር መቆጠር የለበትም። ኤድስን ሰውም ይሥራው የሰማይ ቁጣም ይሁን ከዘመናችን ክፉ መቅሰፍቶች አንዱ መሆኑ እሙን ነው። እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ መሆኑን ሳንዘነጋ ኤድስን እንደ ሕመም ወይም እንደ ደዌ ካየነውና ፈውስ ተደረገ ከተባልን እነዚያ ተፈወሱ የተባሉ ሰዎች እንደዋዛ ከመደባለቃቸው በፊት ማረጋገጥና ማረጋገጫ መጠየቅ እንደ ከሃዲነት ወይም እንደ እምነት አፍራሽነት መታየቱ አግባብ አይደለም። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ከላይ በኬንያው ጋዜጣም

---

41 *“Outlaw These Miracle Merchants” : The Nation (Kenya), Sep, 29, 2001.*





እንደ ምሳሌ የተጠቀሰው በሉቃ. 5፥12-14 ያለው የጌታ የፈውስ አገልግሎት ክፍል ነው። ይህን ክፍል ከመጠነኛ ማብራሪያ ጋር እንመልከተው።

> *12፥ ከከተማዎችም በአንዲቱ ሳለ፣ እነሆ፣ ለምጽ የሞላበት ሰው ነበረ፤ ኢየሱስንም አይቶ በፊቱ ወደቀና፣ ጌታ ሆይ፣ ብትወድስ፣ ልታነጻኝ ትችላለህ ብሎ ለመነው።*
>
> *13፥ እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፣ እወዳለሁ ንጻ አለው፤ ወዲያውም ለምጹ ለቀቀው።*
>
> *14፥ እርሱም ለማንም እንዳይናገር አዘዘው፣ ነገር ግን፣ ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፣ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ስለመንጻትህ ሙሴ እንዳዘዘ መስዋዕት አቅርብ አለው።*

ጌታ በገሊላ አካባቢ ካሉት ከተሞች በአንዲቱ ሳለ አንድ ለምጻም መጣ። እንደዛሬው ሁሉ በዚያን ዘመን እስራኤልም ሁለት ዓይነት ለምጽ ነበረ። አንደኛው የቆዳ ለምጽ ነው። የላይኛውን የቆዳ ቀለም እየበላ የሚሰፋ፣ ጥቁርና ጠይሞችን ቀይ፣ ቀዮችን ደግሞ ነጭ የሚያደርግ የቆዳ በሽታ ነው።

ሁለተኛው ግን ከቆዳ አልፎ ወደ ሥጋ ውስጥ የሚገባ ከሰውነት ጫፎች በአንዱ ወይም በጥቂቱ፣ በእጅ ወይም በእግር ጣት፣ በአፍንጫ፣ በጆሮ ጫፎች ይጀምርና ወደ መሐል እየሰረሰረ የሚሄድ፣ ሥጋን ሁሉ እየበላ የሚዛመት የነርቭ በሽታ ነው። ጣቶች አልቀው የእጅ ወይም የእግር ጉቶ ብቻ እስኪቀር ድረስ የሚጎምድ፣ የሚቆምጥ በሽታ ነው። የዚህ በሽታ ዋና ክፋት ነርቮችን ስለሚገድል በሽተኛው ሕመሙ አይሰማውም። እየቆሰለ፣ እየተቆረጠ፣ እየተወጋ ምንም አይሰማውም። በሕይወት እያሉ አካል ማለቅ፣ መሞት ይጀምራል። ቁምጥና የሚባለው ይህ በሽታ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ግን ሁለቱም ለምጽ ተብለው ነው የተጠሩት። ለምጽን ወይም ቁምጥናን በተመለከተ በብሉይ ኪዳን የተሰጠ ሰፊ ሕግ ይገኛል። ከድንጋጌዎቹ መካከል አንዱ ከማኅበረ ሰቡ እንዲለይ የሚያዘው ነው። በተለይ ዘሌ. 13፥45-46 ልብሱ የተቀደደ፣ ራሱ የተገለጠ፣ ከንፈሩ የተሸፈነ እንዲሆን፣ ሰው እንዳይቀርበውና እንዳይነካው ለማስጠንቀቅ፣ “ርኩስ ርኩስ ነኝ” እያለ እንዲናገር፣ መኖሪያው ከሰፈር ውጭ ሆኖ ብቻውን እንዲኖር ያስጠነቅቃል። ከኅብረተ ሰቡ ወጥቶ፣ ከቤተ ሰብ ተለይቶ፣ ተሰድዶ ለብቻው ይኖራል። የማንም ትከሻ አይገፋውም፤ የማንም እጅ አይዳስሰውም። ተጋፍቶ መኖር ትልቅ በረከት መሆኑን የሚያውቅ ሰው ነው። ይህ ለምጽ ወይም ቁምጥና ኃፍረት፣ ፍርሃትና ድንጋጤ የሞላበት በሽታ ነው። ጥንትም ዛሬም እንደሚነገረው እነዚህን በሽተኞች የሚጎዳቸው ከአካላዊው ጉዳት ይልቅ ኅሊናዊው፤ ስነ ልቡናዊው ስቃይ ነው። ሰው ሁሉ ሲያያቸው የሚዘገንነው፣ የማይቀርባቸው፣ የማይነካቸው፣ ከሩቅ

የሚሸሻቸው ናቸው። ለእንደዚህ ያሉ ሰዎች ሰዎችን ከመንካትና በሰዎች ከመነካት የበለጠ ምንም የሚያስደስታቸው ነገር የለም።

እንዲህ ያለው ለምጻም ሰው ነበር ወደ ኢየሱስ የመጣው። ይህ ሰው በቆዳው ለምጽ ሳይሆን በቁምጥናው ለምጽ የተያዘ ነው። ለምጻም ሳይሆን ለምጽ የሞላበት ነው የተባለው። ይህ ሰው ሊነካው ቀርቶ ማንም የማይቀርበው ዓይነቱ ለምጻም ነው። ስለ ኢየሱስ የነበረው እውቀት ግን በቂ ነበር። ‘መምህር ሆይ’ ሳይሆን ‘ጌታ ሆይ’ ነበር ያለውና የጌታን ጌትነት ያወቀ፥ ያመነና የተቀበለ ይመስላል። ይህ ሰው አንድ ሌላ ነገርም የተረዳ ይመስላል። ኢየሱስ ሊያነጻው እንደሚችል ወይም ችሎታ እንዳለው አውቆአል ግን ሊያነጻው እንደሚወድ እርግጠኛ አይመስልም። በእግዚአብሔር ዘንድ መቻልና መውደድ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እርሱ ሁሉን ቻይ ነው። ሁሉን ማድረግ ይችላል። የሚችለውን ሁሉ ግን ያደርጋል ወይም ሊያደርግ ይወድዳል ማለት አይደለም። ለምሳሌ፥ እግዚአብሔር መፈወስ ይችላል፤ ነገር ግን መፈወስ ይችላል ማለት ፈቃዱ ሁሌ ፈውስ ነው ማለት አይደለም። የፈቃዱን እውቀት የማወቅ አስፈላጊነት እዚህ ላይ ነው። ወደ ኢየሱስ መጣና በፊቱ ወድቆ ጌታ ሆይ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ አለው። ጥያቄ አይደለም። ብትወድ፥ ብትፈልግ ትችላለህ ማለቱ ነው። ይህ ሰው የማይቀርበውና ወደ ሰው መቅረብ የሌለበት ሰው ነው። ሁሉ የሚጸየፉት ይህ ሰው ሰውን ሁሉ አልፎ ወደ ኢየሱስ መጣና በፊቱ ወደቀ።

እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፥ እወዳለሁ ንጻ አለው፤ ወዲያውም ለምጹ ለቀቀው። በብሉይ ሕግ ለምጻምን መንካት ርኩስን መንካት ነው። ርኩስን መንካት መርከስ ነው። አይሁድ ላለመርከስ በጣም ይጠነቀቃሉ። ጌታ ግን ነካው። ዳሰሰው። የማይነካውን ነካ! መንካት ብቻ አይደለም፤ ሰዎች ሁሉ እጃቸውን ወደሚሰበስቡበት ሰው እጁን ዘረጋና ዳሰሰው። እወዳለሁ ንጻ ብሎ ቃልን ተናገረ። ሳይነካው ቃልን ብቻ መናገሩ ሊፈውሰው ይችል ነበር። እርሱ ግን ከዚያም ያለፈ አደረገ። በጌታ ዘንድ ፍቅር ከሕግ በላይ ነው። የዳሰሰው ሕጉን ለመሻር ሳይሆን ፍቅርን ለመግለጥ ነው። ለፈውሱ ቃልን መናገሩ በቂ ቢሆንም የሰውየውን ጥልቅ የፍቅር ናፍቆት፥ የመዳሰስ ፍላጎት ግን ቃልን መናገሩ አይደርስም። ስለዚህ ይህንን ለመድረስ ዳሰሰው። ይህ ከቆዳውና ከሥጋው ያለፈ የልብ ቁስል ፈውስ ነው። እሱና ጌታ የሚያውቁት የውስጥ ፈውስ ነው። ኋላ ሄዶ ራሱን ለካህን ቢያሳይም ካህኑ የተፈወሰ ሥጋውን እንጂ የተጠገነ ልቡንና ሙሉ የሆነ እሱነቱን አያይም። ይህ ድንቅ ጌታ ነው። ይህ ድንቅ እውነት ነው። ዛሬም ያልተለወጠ ባህርዩ ነው።

እርሱም ለማንም እንዳይናገር አዘዘው፥ ነገር ግን፥ ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፥ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ስለመንጻትህ





ሙሴ እንዳዘዘ መስዋዕት አቅርብ አለው። በመጀመሪያ ለማንም እንዳይናገር አዘዘው። ይህን ያለው ምናልባት ወሬው ያለልክ ተዛምቶ የወሬና ተአምር የማየት ናፍቆት ያላቸው ሰዎችን ስብሰባ ለማስቀረት ይሆን? ቀጥሎም ራሱን ለካህን እንዲያሳይና መስዋዕት እንዲያቀርብ አለው። ይህ መስዋዕት በዘሌ. 14 የተጠቀሰው ነው።

ራሱን ለካህን ማሳየቱ አስፈላጊ ነበር። ካህን በብሉይ ኪዳን የፈውስ አስረጋጭ፥ ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ፥ መፈወሱን የሚያረጋግጥ፥ ወይም በዘመናዊ ቋንቋ ነጻ ነው የሚል የምስክር ወረቀት እንደሚሰጥ ሐኪም ነው። ለምጹ መጥፋቱ በሰውነቱ ይታያል። ግልጽ ነው። ማኅበረ ሰቡ ግን ሊቀበለው ይከብደዋል። አሁንም ለምጻም ይመስለዋል። ኢየሱስ በሽታውን ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ግንኙነቱንም ሊፈውስ ወደ ካህን ላከው።

አንዳንድ ሰዎች ከተፈወሱ በኋላ ሄደው ሐኪም እንዲያዩ ሲነገራቸው አገር ጥለው መጥፋት ያሰኛቸዋል። ለምን ሲባሉ እምነት ማጣት ይመስላቸዋል። የፈወሱአቸው ሰዎች ስለ እምነት ረቂቅና የማይጨበጥ ትምህርት ሰጥተዋቸዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንም እንዲህ ያለ ነገር ባናገኝም ፈውሰኞቹ ተፈዋሾቹን ከተጠራጠሩ በሽታው እንደሚመለስባቸው ያስፈራራሉ። ስለዚህ ወደ ሐኪም ሄዶ መፈወስን ማረጋገጥ በደል መስሎአቸው ተፈውሰሃል ተብለው፥ ተፈውሻለሁ ብለው ይኖራሉ። በድንገትም ይሰናበታሉ። ምን ሆነ? ሲባል ወደ አምላኩ ተሰበሰበ ይባላል። እርግጥ በክርስቶስ ካመነ ወደ አምላኩ ተሰብስቦአል። ግን ምን ሆኖ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ አይሰጥም። ጥያቄው እንዲነሣም አይፈለግም። ስለዚህ ያልተፈወሱ ተፈወሱ ሲባል ጠንቃቃ እንሁን። ይህ አሳብ በቀደመው መጽሐፍ የፈውስ ቀውስ ስር ብዙ ተብሎበታል።

በጌታ የተፈጸመው ተአምር ምንም ያልጎደለው ተአምር ነው። አድራጊው ደግሞ ራሱ ጌታ ነው። ከተፈወሰ ተፈውሰሃል ብቻ ብሎ ለምን አልተወም? ለምን ሄዶ ራሱን ለካህን እንዲያሳይ አለው? ምክንያት ነበረው። ድውዩ ለራሱ ተፈውሶአል፤ ለሌላውም ፈውሱን ማረጋገጥ አለበት። ፈውስ የሆነላቸው ሰዎችም በሰውነታቸው አውቀውታል። አንዳንዱ ፈውስ ግን ዝም ብሎ ከመደባለቅ በፊት ሌላ ማረጋገጫ ይፈልጋል። ያለጥርጥር ኤድስ ከነዚህ አንዱ ነው።